‹‹ማኅበረ ቅዱሳን›› እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን ስያሜ አግኝቷል።



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰ/ት/ቤቶች ማ/መ
ማኅበረ ቅዱሳን
ኅትመት ሚዲያ መምሪያ
የሚታተም
ትምህርታዊ መጽሔት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ

፳፱ኛ ዓመት ቁጥር ፬
ታኅሣሥ ፳፻፲፬ ዓ.ም.

# ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ም/ዋና አዘጋጅ፡-
*ዲያቆን አሸግሬ አምጤ*
አድራሻ፡- የካ ክፍለ ከተማ
*ወረዳ 01/02 የቤት ቍጥር 521/522*
*+251- 911361580*
ከፍተኛ ሪፖርተር፡-
*ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን*
የገጽ መልክአ ባለሞያና ጸሐፊ፡-
*ገነት ታደሰ*
አሳታሚበማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት አስተዳደር
*አ.አ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06*
የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ፡-
*+251-118-124222*
*ፖ. ሣ. ቍ.80078*
*magazine@eotcmk.org*
የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት
*+251-962 17 17 17*
የልማት ተቋማት ሽያጭና ስርጭት መምሪያ
*0111 54 04 84/24 61 84/944 25 90 14*
የገበያ ጥናት አገልግሎት መምሪያ
*0111266549/942 38 17 91/944 25 90 26*

## ማውጫ

**መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን**
ዘመኑ በጋራ የምንቆምበት ነው................................... ፪

**ዐውደ ስብከት**
ሰላም የሕይወት ማጣፈጫ ቅመም ...............................፬

**ትምህርተ ሃይማኖት**
ኦ ከርሥ ዘተጽሕፈ ውስቴታ መጽሐፈ ግእዛን ለኵሉ ሰብእ (ሃ.አበ.፵፰፥፲፭) ..................................................፯

**ዐብይ ጉዳይ**
የተቸገሩትን በመርዳት በረከትና የአእምሮ ሰላም እናግኝ....................................................................፲

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**
አርአያነት ተግቶ በመሥራት....................................... ፲፬

**እናስተዋውቃችሁ**
ብሔረ ብፁዓን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም....................... ፲፯

**የነገዋ ቤተ ክርስቲያን**
ደቀ መዝሙርነት....................................................፳

**ኪነ ጥበብ**
ጸልዩ....................................................................፳፫

**የጥያቄዎቻችሁ መልስ** .............................................፳፮

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ፡፡*

# ዘመኑ በጋራ የምንቆምበት ነው

የምንገኝበት ዘመን መከራ የበዛበት በመሆኑ ከመቼውም ጊዜ በላይ መተባበርና መደጋገፍ የሚጠይቅ ነው፡፡ መከራ ሲገጥመን መተባበር እንደሚኖርብን የማንም ማሳሰቢያና ማባበያ አያስፈልገንም፡፡ በአገራችን እየደረሰ ያለው መከራ ሊያስተባብረን ካልቻል ሌላ የሚያፋቅረን ነገር ማግኘት አንችልም፡፡ የምንኖርባትን ዓለም ጣዕም የቀየሩት ራሳቸውን ብቻ ለማትረፍ ሲደክሙ የኖሩት ሳይሆኑ በመተባበር ለመከራ የተዳረጉትን ሰዎች ሕይወት ሲታደጉ የኖሩት መሆናቸውን መገንዘብ ይገባል፡፡ ከመለያየት ይልቅ መተባበር፣ ከመቀበል ይልቅ ለተቸገሩት መስጠት የቻሉት የሰው ፍቅር የበለጠባቸው፣ ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸው ለችግር ለተጋለጡትም የሚያስፈልጋቸው መሆኑን የተረዱ ናቸው፡፡ መስጠት ደስታን ሲሰጥ መቀበል ኃፍረትን ያላብሳል፡፡ መተባበርና መደጋገፍ ኃይል ሲፈጥር መለያየት ደግሞ አገርን ስለሚያዳክምና ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ መልካም ነው ተብሎ የተነገረውን ስለሚቃረን መተባበር ይገባል፡፡

ዘመኑ መደጋገፍና መረዳዳት የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳት ከራስ ወዳድነት መላቀቅ ታላቅነት ነው፡፡ ቀያቸውን ለቀው የተሰደዱ፣ ሀብት ንብረታቸውን አጥተው በችግር የሚሰቃዩ፣ ወገኖቻቸው አልቀው በኀዘን የተጨበጡ ወገኖቻችን ቍጥር ከሚሊዮን በላይ ሆኗል፡፡ የተቸገሩትን መርዳት ሃይማኖታዊ ግዴታችን፣ ሥነ ምግባራዊ መገለጫችን መሆኑን ተረድተን ከሌሎቹ ቀድመን ለተቸገሩ ወገኖቻችን መድረስ የሚገባን ክርስቲያኖች ነን፡፡ አገራችን ሰላም ውላ እንድታድር ታላቅ ኃላፊነት እንዳለብን መዘንጋት የለብንም፡፡ መልካም በማድረግ የተጎዱትን የምንደግፈው በሌሎች ላይ የደረሰው መከራ እንዲደርስብን ስለማንፈልግ ብቻ ሳይሆን ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ በአምላኩ ዘንድ የሚመሰገን በመሆኑ ጭምር ነው፡፡

የሃይማኖት ልዩነት ሳንፈጥር ለተቸገሩ ወገኖቻችን ስንደርስላቸው በአንድ በኩል ክርስቲያናዊ አስተምህሯችን ለሌሎች ይገለጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ክርስቲያኖች የተቸገሩትን በመደገፋችን የሞራል ልዕልናችንን ዓለም ያውቀዋል፡፡ ሰዎች ሲቸገሩ ዓይተው የሚያዝኑ ክርስቲያኖች ንዑዳን ክቡራን ተብለው ተመስግነዋል፡፡ ወገኖቻችን አገር ለቀው ተሰደው፣ ቀያቸውን ትተው ተፈናቅለው እያየን ለእነርሱ የምናደርገው ድጋፍ ብቻ ሳይሆን ለእነርሱ ማዘናችን ንዑዳን ክቡራን ያሰኘናል ማለት ነው፡፡ በእርግጥ ክርስቲያኖች ለተቸገሩ ወገኖቻችን ሁሉ መልካም የምናደርገው ሰዎች ያመስግኑን፣ ንዑድ ክቡር ይበሉን ብለን አይደለም፡፡ ሰዎችን መደገፋችን አምላካችንን ስለሚያስደስተው ክርስቲያኖች በዚህ ምድር ስንኖር አምላካችንን የሚያስደስት በጎ ምግባር መፈጸም ስላለብን ነው፡፡ መከራ ሲመጣ ደግሞ የበለጠ መተባበርና መደጋገፍ ይኖርብናል፡፡ የተፈጠርንለት ዓላማ ሠርተን ያገኘነውን ራሳችን በልተን እንድንደሰት ሳይሆን ሠርተን ካገኘነው ለሌላቸው ወገኖቻችን እንድናካፍል፣ ተባብረን ወገኖቻችንን ከሞት እንድንታደግ ነው፡፡ ተጋግዘን ለተቸገሩ ወገኖቻችን በመድረስ ሕይወታቸው እንድትቀጥል፣ ዕድሜ ለንስሓ ዘመን ለፍስሓ እንዲያገኙ ስናግዛቸው ደስታችን ፍጹም ይሆናል፡፡

በሃይማኖት የሚመስሉን ብቻ ሳይሆኑ የማይመስሉን ወገኖቻችንም በደረሰባቸው ችግር ምክንያት አገር ለቀው ሲሰደዱ፣ በስደት ወደ አሕዛብ አገር ሲሄዱ መታደግ ከክርስቲያኖች ሁሉ የጠበቅ ተግባር ነው፡፡ ለወገኖቻችን ራሳችንን ዐሳልፈን ለመስጠት የሚያስችል መንፈሳዊ ጥብዓት ባይኖረን እንኳ ከገንዘባችን ከፍለን ለተቸገሩ ወገኖቻችን መደገፍ ከሚጠበቅብን ክርስቲያናዊ ትሩፋት ትንሹ ነው፡፡ እስከ ሞት ድረስ የተቸገሩትን

በመርዳት መታደግ፣ ሰውን ሁሉ መውደድ እንደሚገባን የተነገረን ለራሳችን ከሚያስፈልገን ቀንሰን ሌሎችም እንደሚያስፈልጋቸው አምነን እንድንረዳቸው ነው።

እውነተኛ ወገን የሚታወቀው በመከራ ዘመን በመሆኑ አገር ለቀው ለተሰደዱ፣ በችግር አሽክላ ታስረው ለሚሰቃዩ፣ ረሃብና ኀዘን ተጨምሮባቸው ለሚንገላቱ ወገኖቻችን በመድረስ አለኝታነታችንን በተግባር እናሳያቸው። ከመንፈስ ልዕልና የደረሱት ሰዎች ለራሳችን ይቅርብን ብለው ወገናቸውን ሲያስቀድሙ እኛ ደግሞ ቢያንስ ካለን በማካፈል ለወገን አለኝታነታችንን እናረጋግጥ። በዘመናችንም ቅዱሳን ከፈጸሙት ያልተናነሰ ተግባር በመፈጸም ላይ የሚገኙ ክርስቲያኖች መኖራቸውን የሚገልጠው ጦርነት በተካሄባቸው አካባቢዎች የሚገኙ አበው ሊቃነ ጳጳሳት እና ምእመናን የፈጸሙት ተግባር ነው።

በጦርነት ምክንያት ቀያቸውን ለቀው የተሰደዱትን፣ በልዩ ልዩ ምክንያት ለችግር የተጋለጡትን ወገኖቻችንን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የቋንቋም ሆነ የመልክአ ምድር ልዩነት ሳናደርግ መርዳት ከክርስቲያኖች ሁሉ የሚጠበቅ በጎ ተግባር ነው። በአሳብ አንድ ሆነን የወገን ፍቅር በልጥብን ተባብረን የተቸገሩትን ከደገፍን "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ"፤ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤ በተራራ ላይ የተሠራች ከተማ መሰወር አይቻላትም" ተብሎ የተነገረውን በተግባር ፈጸምን ማለት ነው። በክርስቲያናዊ ምግባራችን አልጫውን ዓለም ማጣፈጥ፣ ጨለማውን ዓለም ማብራት ሲገባ ገብር ሐካይ መሆን የለብንም።ክርስቲያኖች የተራራ ላይ ብርሃንና የምድር ጨው መሆናችን የሚገለጠው ሠርተን ካገኘነው ለወገኖቻችን ስንተርፍ ነው።

ሰዎች ለመከራ በተጋለጡበት ዘመን የተቸገሩትን መረዳት ለተረጅዎች የሚኖረውን ጠቀሜታ ቃላት የመግለጥ አቅም የላቸውም። ተባብረን ወገኖቻችንን ስንረዳቸው ተጎጂዎች የሚያስብልን ወገን አለ ብለው ተስፋቸው ይለመልማል፤ ዙሪያው ገደል የሆነባቸው መውጫ መንገዱ ይታያቸዋል። ተስፋቸው መለምለም ብቻ ሳይሆን ተፈናቃዮች በደረሰባቸው መከራ ምክንያት በረሃብ እንዳያልቁ ያደርጋል። ልጆቻቸው ተርበው ሲያለቅሱባቸው ተስፋ ቆርጠው አምላካቸውን እንዳይክዱና ሃይማኖታቸውን እንዳይለውጡ የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ በመተባበር ወገኖቻችንን መርዳት ይኖርብናል። ተፈናቃዮች ዕድሜ ልካቸውን በሰው ድጋፍ ሳለመኖርና ሠርተው ተለውጠው ራሳቸውን በመቻል ሌሎችን እንዲረዱም ተግባራዊ ትምህርት ያገኙበታል ብለን እናምናለን።✥

# ሰላም የሕይወት ማጣፈጫ ቅመም

**ዲ/ን ተስፋዬ ምትኩ**

ሰላም በስምምነትና በአንድነት፣ በፍቅርና በደስታ ከሌሎች ጋር አብሮ መኖር ነው:: ሰላም ስምምነት ነው ስንል ግን የዕቅድና የዓላማ፣ የእምነትና የባህል፣ የሃይማኖትና የመንፈሳዊ ሕይወት፣ የትምህርትና የሥራ ዘርፍ ተመሳሳይነት ካላቸው ሰዎች ጋር ብቻ የሚደረግ መስማማት አይደለም::በተለይ በአርባ እና በሰማንያ ቀን ተጠምቀን፣ የሥላሴን ልጅነት አግኝተን የክርስቶስ አካል፣ የቤተ ክርስቲያን አባል ሆነን በወልድ ውሉድ፣ በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳውያን፣ በክርስቶስም ክርስቲያን ለተባልንና ለሆንን ለእኛ ከሁሉ ጋር በሰላም እና በስምምነት መኖር መንፈሳዊ ግዴታችን ነው::ክርስቶስ ሁሉን እኩል አድርጎ እንደ ወደደ፣ ከሚሰድቡትና ከሚነቅፉት ብሎም፣ ሊገድሉት ከሚፈልጉት ጭምር በመካከላቸው እንደ ኖረ፣ አላዋቂዎችን በማስተማር፣ ስሑታንን በመምከር፣ አመፀኞችንም በመገሠጽ ከመልካም አባት የሚጠበቀውን ተግባር እንደተወጣ እኛም አርአያውን መከተል ይኖርብናል::

ከሁሉ ጋር በሰላም አብረን እንድንኖር ብንታዘዝም ከክፉ ሥራዎቻቸውና ከከንቱ እምነታቸው ግን ተባባሪ መሆን የለብንም::ከቻልን በቃልና በተግባር አስተምረናቸው እኛ ወደ ያዝነው እምነትና እውነት እንዲመጡ ማገዝ፣ ካልቻን ደግሞ መተባበር ባለብን ጉዳይ ብቻ እየተባበርን በቀሩት ጉዳዮች ተከባብረን መኖር ይጠበቅብናል::ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ "ቢቻላችሁስ ከእናንተ በኩል ከሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ" በማለት ያስተማረን (ሮሜ. ፲፪፥፲፰)::

"ከሁሉ ጋር" የሚለው ቃል ከሚመስሉንም ከማይመስሉንም ጋር አብረን መኖር መንፈሳዊ ግዴታችን መሆኑን ያስገነዝበናል:: ቢቻላችሁስ ሲልም ካልቻላችሁ ራቁአቸው ለማለት እንጂ ካልቻላችሁ ተጣሉ ማለት አይደለም:: የምንርቀውም ከክፉ አሳባቸውና ተግባራቸው እንጂ ከሰዎቹ መሆን የለበትም:: "ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ" የተባለው ለዚህ ነው (፩ኛ. ተሰ.፭፥፳፪):: ክርስቶስ ኃጢአትን እንጂ ኃጢአተኞችን መጥላት እንደ ሌለብንና መራቅም እንደ ማይገባን ያስተማረን ለዚህ ነው::

### የሰላም አስፈላጊነት

ሰላም የሰው ልጅ በዚህ ምድር ለመኖር እጅግ ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነገሮች አንዱ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ "የሰው የፊቃዱ ሁሉ መጀመሪያ ውኃ፣ እሳት፣ ብረት፣ ጨው፣ እህል፣ ስንዴ፣ ማር፣ ወተት፣ ወይን፣ ዘይትና ልብስ ነው" በማለት ስለመሠረታዊ ፍላጎቱ ይናገራል (ሲራ.፴፱፥፳፮):: ለሰው ልጅ ከዕለት ጉርስና ከዓመት ልብስ በላይ የሚያስፈልገው መሠረታዊ ጉዳይ ሰላም ነው:: ሰላም ከሌለ ወጥቶ መግባት፣ ሠርቶ መብላት አይቻልምና:: ሰው ነግዶ ትርፋማ፣ አርሶ ምርታማ፣ ተምሮና ተመራምሮ ውጤታማ መሆን የሚችለው ሰላም ሲኖር ብቻ ነው:: ሰላም ከሌለ እንኳንስ ማረስና ማምረት፣ መነገድና ማትረፍ ቀርቶ ተጋግሮ የተዘጋጀውን ቆርሶ መመገብ፣ ተሰፍቶ የተዘጋጀውን ልብስ ለብሶ ማጌጥ፣ በኪስ ያለውን ገንዘብ ለሚያስፈልገው ጉዳይ መጠቀም የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል::

ሰላም በሌለበት ለብሶ ማጌጥ፣ በልቶ መጥገብ፣ ጠጥቶ መርካት፣ ተናግሮ መሰማት የለም:: ይህ ሁሉ የሚያስረዳን ሰላም ከሁሉ በላይ አስፋለጊ ጉዳይ መሆኑን ነው:: ለዚህም ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ የሰጠውን ስጦታ ዘርዝሮ መጨረስ ባይቻልም ከብዙዎቹ አንዱ ሰላም መሆኑን "ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜንም እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጠው አይደለም፤ ልባችሁ አይደንግጥ፤ አትፍሩም" በማለት ያጽናናቸው (ዮሐ.፲፬፥፳፯):: ደቀ መዛሙርቱ የቤታቸውን በር ዘግተው በብዙ ጭንቀት በነበሩበት ጊዜ በመካከላቸው ተገኝቶ ያጽናናቸው "ሰላም ለእናንተ ይሁን" በማለት ነበር(ሉቃ.፳፬፥፴፮፤ ዮሐ.፳፥፲፱-፳፮)::

ዛሬም የክርስቶስ ማደሪያ የሆነቸው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጸሎተ ቅዳሴ ደጋግማ የምትጸልየውና የምትሰብከው ስለሰላም ነው::ስለ ሀገር፣ ስለ ሕዝብ፣ የሀገርን ዳር ድንበር ስለ ሚጠብቀው የሀገር ሠራዊት፣ ስለሚያርሱ፣ ስለሚነግዱ፣ ስለሚገዙ፣ ስለ ተሰደዱ፣ በግፍ ስለታሰሩ ወዘተ. እግዚአብሔር ሰላምን እንዲያበዛላቸው ትጸልያለች::"በእንተ ቅድሳት" በተሰኘው የጸሎት ክፍል ዲያቆኑ ከመነሻው "አንድ ስለምታድርግ ሥጋውና ደሙ እግዚአብሔር ይቅር ይለን ዘንድ ሰላምን እንማልዳለን" ብሎ በመጀመር በመጨረሻው "በጸሎት የምንለምንና የምንማልድ ሁላችንንም በሰላም በፍቅር ይጠብቀን" ብሎ እስኪደመድመው ድረስ ያለው ጸሎት ሰላምን፣ ፍቅርን፣ አንድነትን የሚመለከት ጸሎት ነው::

በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ በዕለተ ዓርብ ጌታ በመልዕልተ መስቀል ነፍሱን ከሥጋው በፈቃዱ ለይቶ በሥጋው ወደ መቃብር፣ በነፍሱ ደግሞ ወደ ሲኦል ወርዶ በዚያ ከነበሩ ነፍሳት ጋር እንደ ተነጋገረ ዲያቆኑ አዳምን ወክሎ "ተንሥዑ ለጸሎት፡- ለጸሎት ተነሡ" ሲል ሕዝበ ክርስቲያኑ ደግሞ ነፍሳትን በመወከል "እግዚኦ ተሰሃለነ፡- አቤቱ ይቅር በለን" ይላሉ:: ካህኑ ክርስቶስን ወክሎ "ሰላም ለኵልክሙ፡- ሰላም ለሁላችሁ ይሁን" ሲል ሕዝበ ክርስቲያኑ መልሰው "ምስለ መንፈስከ፡- ከመንፈስ ጋራ" በማለት ይቀበሉታል::ይህ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ለሰላም ያላትን ዋጋ የሚያሳይ ነው::

በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት የሰው ልጅ በዋናነት ከሦስት ነገሮች ጋር ሰላም መፍጠር ይኖርበታል:: እነዚህም ከራሱ ሕሊና ጋር ከፍጥረታት ሁሉ በተለይም ከሰው ልጆች ጋር በዋናነት ደግሞ ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር ስምምነት መፍጠር ይገባዋል:: እነዚህን ሦስት ነገሮች በአጭሩ እንደሚከተለው እንመለከታለን::

## ከራስ ሕሊና ጋር ሰላም መሆን

የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ተለይቶ አራቱ ባሕርያተ ሥጋና ሦስቱ ባሕርየ ነፍስ ያለው ፍጡር ነው።ሥጋና ነፍስ እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም" በማለት የገለጠው ለዚህ ነው (ገላ.፭፥፲፯)።ሁለቱ ፈቃዳት አንዱ ሌላውን አሸንፎ ፍላጎቱን ፈጽሞ ለማርካት በሚያድርጉት እሽቅድድም ውሳኔ ለመስጠት በመቸገር የሰው ልጅ ሲያወጣና ሲያወርድ ሰላምና መረጋጋትን ያጣል፣ ይጨነቃል፤ ይረበሻል፤ ሰው ለፈቃደ ሥጋ ተሸንፎ ከፈቃደ እግዚአብሔር ጋር የሚቃረን ተግባር ሲፈጽም እውነተኛው ዳኛ ሕሊና እየወቀሰ ሰላም ይነሣዋል።

ሕሊና ስናጠፋ የሚከሰን፣ መልካም ስናደርግ የሚመሰክርልን ሚዛናዊ ዳኛ ነው። ሰው መልካም ሲሠራ አመስጋኙ ብዙ ነው። ክፉ ሲሠራም ወቃሹ ቀላል አይደለም። ሆኖም ግን ክፉ ሥራ በይፋ በአዳባባይ ስለማይሠራ በብዙ ሰዎች ዘንድ የመታወቅ ዕድሉ አነስተኛ ነው። ሕሊናችን ግን ከሰዎች ተደብቀን የሠራነውን ሁል ጊዜ እያሳሰበ ሲከሰን ይኖራል። ለፈጸምነው ጥፋት ልክ እንደ አዳም ምክንያት ብንደረድር እንኳ ተግባራችን ትክክል አለመሆኑን እየገለጠ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እውነት የሆነውን እየነገረ ንስሓ እስክንገባ ድረስ ያስጨንቀናል፤ ከእውነት ርቀን፣ ጸጋ እግዚአብሔርን ተገፍፈን፣ ርቃናችንን መሆናችንን እየነገረ አዳም በሕሊና ጭንቀት ይናወጥ እንደ ነበር በጽኑ ጭንቀት እንድንዋጥ ያደርገናል። አዳም ለጊዜው ምክንያት አላጣም ነበር። ይሁን እንጂ ምክንያቱ ከሕሊና ወቀሳም ሆነ ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያድነው አልቻለም። ዛሬም ብዙዎቻችን ጥፋታችንን ከሰው ለመሰወር ብዙ ጥረት እናድርጋለን። ከሕሊናችን መሰወር ስለማንችል እየተሳቀቅን ለመኖር እንገደዳለን። አላፊ አግዳሚው ሁሉ በደላችንን ያወቀብን እየመሰለን ከመቼ፣ መቼ ይገለጥብኛ ይሆን እያልን እንረበሻለን፤ በተለይ እውነት ከሚነገርባቸው ዐውደ ምሕረቶች፣ እውነትን ካስተማሩን አባቶች፣ እውነትንና እምነትን ካስተዋወቀችን ቤተ ክርስቲያን ለመሸሸግ እንጥራለን።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ወንድሙን የገደለው ቃየል ነው።ቃየል ወንድሙን አቤልን የገደለው ማንም ሳያየው ብቻውን ሆኖ ነበር።ከእግዚአብሔርና ከሕሊና ሊሰወር የሚችል የለምና እግዚአብሔር "ወንድምህ አቤል ወዴት ነው" ብሎ ጠየቀው።ቃየል ግን "እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን" ብሎ ወንድሙ የት እንዳለ እንደማያውቅ መልስ ሰጠ። እግዚአብሔርም "የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፏን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ።ምድርንም ባረስህ ጊዜ ኃይሏን አትሰጥህም፤ በምድርም ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ ትሆናለህ" በማለት ረገመው። ቃየል በዚያን ጊዜ ሊሸሽገው ያልቻለውን የሕሊናውን ክስ "በምድር ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ፤ የሚያገኘኝ ሁሉ ይገድለኛል" በማለት ስለራሱ መሠከረ (ዘፍ.፬፥፰-፲፬)።

በዘመናችን ቃየል የፈጸመውን እኩይ ተግባር የሚፈጽሙ ብዙ ናቸው።ለእግዚአብሔር ቃል፣ ለቤተ ክርስቲያን አደራ፣ ሕዝብ ለሰጣቸው ኃላፊነት ሳይታመኑ ቀርተው በስውር የሠሩትን ሰው ያወቀብን እየመሰላቸው በሕሊና ወቀሳ ዕረፍት የሚያጡት በጣም ብዙ ናቸው።ለዚህ ሁሉ መፍትሔው ኃጢአትን ለካህን በመናዘዝ አማናዊውን ሰላም አግኝተን ከሕሊና ወቀሳና ከተቅበዝባዥነት ነጻ መውጣት ነው።

## ከፍጥረታት ሁሉ ጋር በሰላም መኖር

የሰው ልጅ በምድር የሚኖሩ ፍጥረታትን ሁሉ ይገዛና ይነዳ፣ እንዳስፈላጊነቱም ይጠቀም ዘንድ ሥልጣን ተሰጥቶታል (ዘፍ.፩፥፳፯-፴)። ቅዱሳት መጻሕፍትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እንደሚነግሩን አዳምና ሔዋን ከተፈጠሩበት ዕለት ጀምሮ የተሰጣቸውን ሕገ እግዚአብሔርን አፍርሰው ከገነት እስከተባረሩበት ጊዜ ድረስ ከፍጥረታቱ ሁሉ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ሰላማዊ ነበር። እንስሳቱና አራዊቱም ወደ አዳም እየሄዱ "ከእኛ አንዳችንን አርደህ ብላ፣ አልበህ ጠጣ" ይሉ ነበር። አዳም ግን እኔ የሚበላና የሚጠጣ አላጣሁም።ከአንዲት ዕፀ በለስ በስተቀር አምላኬ ሁሉን ሰጥቶኛል።እናንተን ግን አምላካችን ያርባችሁ፤ በሰላም ሂዱ ብሎ ያሰናብታቸው እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስነብበናል (ዘፍ.፫፥፯ አንድምታ)።አዳም ኃጢአት ሠርቶ ከእግዚአብሔር ጋር ሲጣላ ግን ፍጥረታት ሁሉ ከአዳም ጋር ተጣልተዋል። ከፍጥረታት ሁሉ በመጀመሪያ ከአዳም የተጣላችው ምድር ነበረች። እሾህና አሜካላ በቅሎባት፣ አዳም በእሾህ እየተወጋ፣ በእንቅፋት እየተመታ፣ ወጥቶ ወርዶ፣ ጥሮ፣ ግሮ በድካሙ የዕለት ጉርስ ያገኝባት ዘንድ ተፈርዶበታልና። አባታችን አዳም "እግዚአብሔር ሆይ ዛሬ ግን ትእዛዝህን ከተላለፍኩ በኋላ ሁሉም ይበሉኝ ዘንድ ተነሣሡ፤ ..ከገነት እንዳስወጣኸን በኃፌዋ ምድርም እንዳስቀመጥከን አራዊት በእኛ ላይ እንዲሠለጥኑ አትፍቀድላቸው" በማለት የተማጸነው እንስሳትና አራዊት እንደ ቀድሞው አርደህ ብላን ብለው ወደ አዳም ከመቅረብ ይልቅ የሚሸሹት፣ አንዳንዶቹም አደጋ ሊያደርሱበት የሚያሳድዱት በመሆናቸው ነበር (ገድለ አዳም፣ ፳፻፲፩፣ ፴፫ )።።

የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ በላይ ሰላማዊ መሆን የሚገባው ከሰው ልጆች ሁሉ ጋር ብቻ ሳይሆን ከእንስሳትና ከተፈጥሮ ጋር ጭምር ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው እንደ መሆኑ መጠን ከሰው ሁሉ ጋር እንዴት በሰላም መኖር እንደ ሚገባን በቃልም፣ በተግባርም አስመምሮናል። ዘመድና ባዕድ፣ ሀብታምና ድሃ፣ ጻድቅና ኃጢአተኛ፣ ልጅና ዐዋቂ፣ ጤነኛና በሽተኛ ሳይለይ ከሁሉ ጋር አብሮ በመሆን የሚጠሉትን በመውደድ፣ የሚረግሙትን በመባረክ ለሚገደሉትም ጭምር ምሕረትን በመለመን፣ ይቅርታና ምሕረት በማድረግ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላምና በፍቅር እንድንኖር አርአያ ሆኖናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ … ክፉን በመልካም አሸንፉ እንጂ በክፉ አታሸንፉ" በማለት ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም እንድንኖር መክሮናል(ሮሜ. ፲፪፥፲፯-፳፩)።

ሰላምን ለማግኘት ሰላማዊ ከመሆን ውጭ ሌላ አማራጭ የለም፡፡ በተለይ በሐዲስ ኪዳን ለምንገኝ በሰላሙ አለቃ በክርስቶስ ለምናምን ለእኛ ለክርስቲያኖች ክርስቶስ፣ የእኛን ሰላም ለመመለስ፣ የመጣበትን ክስና ፍርድ ሁሉ ባለመከራከር አሜን ብሎ ተቀብሎ ማንንም ባለመበቀል ዋጋ እንደከፈለልን ለምናምን ሰላማችንን ለማረጋገጥ ከሰላማዊ መንገድ ውጭ አመራጭ የለንም፡፡አማራጭ ያለ ቢመስለን እንኳ ባደረግነው ነገር በመጨረሻው ሕሊናችን ስለሚወቅሰን ሰላም ማጣታችን አይቀርም፡፡

**ዛሬም የክርስቶስ ማደሪያ የሆነቸው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጸሎተ ቅዳሴ ደጋግማ የምትጸልየውና የምትሰብከው ስለሰላም ነው፡፡ስለ ሀገር፣ ስለ ሕዝብ፣ የሀገርን ዳር ድንበር ስለ ሚጠብቀው የሀገር ሠራዊት፣ ስለሚያርሱ፣ ስለሚነግዱ፣ ስለሚገዙ፣ ስለ ተሰደዱ፣ በግፍ ስለታሰሩ ወዘተ. እግዚአብሔር ሰላምን እንዲያበዛላቸው ትጸልያለች፡፡**

### ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መሆን

የሰላም ምንጭና መገኛው እግዚአብሔር ነው፡፡ "እርሱ ሰላማችን ነው" ተብሎ ተጽፏልና (ኤፌ.፪፥፲፬)፡፡ ስለሆነም ሰላምን ለማግኘት ከእግዚአብሔር ጋራ መሆን የግድ ነው፡፡ ከእርሱ ጋር መሆን ስንል ፈቃዱን ብቻ ማድርግ፣ ለባሕርዩ ከማይስማማው ከገቢረ ኃጢአት መራቅ ነው፡፡ ይህን ብናደርግ ሰላማችን ይበዛል፣ ጭንቀትና ኀዘን ከእኛ ይርቃል፤ ዕድሜ ከጤና፣ ሀብት ከሰላም ጋር ይታደለናል፡፡ "ልጄ ሆይ ሕጌን አትርሳ፣ በልብህም ትእዛዛቴን ጠብቅ፤ ብዙ ዘመናትና ረጅም ዕድሜ ሰላምም ይጨመርልሃልና" እንዲል(ምሳ.፫፥፩-፪)፡፡ ኃጢአት ስንሠራ ከኖርን በፍጹም ሰላም ሊኖረን አይችልም፡፡ መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት "ከኃጢአቴ የተነሣ ለአጥንቶቼ ሰላም የላቸውም" በማለት የተናገረው ከእግዚአብሔር ተለይቶ መኖር የሚያስከትለውን ችግር ለመግለጥ ነው (መዝ.፴፯፥፫)፡፡

የሰው ልጅ ከኃጢአት ተለይቶ ከእግዚአብሔር ጋራ ከኖረ ሁሉ ነገር ሰላም ይሆንለታል፡፡ እስራኤላውያን ሰላምን ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለባቸው በሊቀ ነቢያት ሙሴ አማካኝነት እግዚአብሔር "በሥርዓት ብትሄዱ ትእዛዛቴንም ብትጠብቁ ብታደርጉትም፡- በምድራችሁም ላይ ሰላምን እሰጣለሁ፣ ማንም ሳያስፈራችሁ ትተኛላችሁ፣ ክፉዎችንም አራዊት፣ ከምድራችሁ አጠፋለሁ፤ ሰይፍም በምድራችሁ ላይ አያልፍም" በማለት ነግሯቸዋል(ዘሌ.፳፮፥፫-፮)፡፡ በሰላም በመኖር እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ተግባር ከፈጸምን ጠላቶቻችን እንኳን ይወዱናል፤ በባዕድ ሀገር፣ በሥጋ ከማይዛመዱን፣ በሃይማኖት ከማይመስሉን፣ በባህልና በልማድ ከማንመስላቸው ጋር እንኳ በሰላም መኖር እንችላለን፡፡ "የሰው አካሄድ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘ እንደሆነ በእርሱና በጠላቶቹ መካከል እንኳ ሰላምን ያደርጋል" ተብሏልና (ምሳ.፲፮፥፯)፡፡

በአጠቃላይ ሰው ከኃጢአት ተለይቶ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ሲጀምር አደገኛ የሚባሉ አውሬዎች እንኳ ጉዳት አያደርሱበትም፡፡ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከአናብስትና ከአናብርት ጋር የኖሩት፣ አቡነ ሳሙኤል "ዘዋልድባ" አንበሳን ጋልበው ለአገልግሎት ይፋጠኑ የነበሩት፣ አቡነ አረጋዊ በዘንዶ ታዝለው ተራራ የወጡት ከሕሊናቸው፣ ከፍጥረታት ሁሉ እና ከእግዚአብሔር ጋር በሰላም ስለኖሩ ነበር፡፡ ነቢዩ ዳዊት "ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል፤ መታመኛዬ እርሱ ነውና" በማለት የዘመረው አማናዊ ሰላም የሚያስገኝ በመሆኑ ነው (መዝ.፸፪፥፳፰)፡፡ ነገሮች የሚበላሹት በዋናነት ከሕሊናችንና ከእግዚአብሔር ስንርቅ በመሆኑ ሰላማችን እንዲመለስልን ወደ ሕሊናችንና ወደ እግዚአብሔር እንመለስ፡፡ ያጣነውን ሰላም እንድናገኝ የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ጥበቃ አይለየን፡፡ አሜን!!✦

# ኦ ከርሥ ዘተጽሕፈ ውስቴታ መጽሐፈ ግእዛን ለኵሉ ሰብእ

(ሃ.አበ.፵፰፥፲፭)

**ቀሲስ ዐብይ ሙሉቀን**

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናገረ። በኋላ ዘመን ግን ሁሉን ወራሽ ባደረገው፣ ሁሉንም በፈጠረበት በልጁ ነገረን" (ዕብ.፩፥፩-፪) ብሏል። "ሁሉን በፈጠረበት በልጁ" የሚለው እግዚአብሔር ወልድ የአብ ኃይሉ፣ ክንዱ መሆኑን የሚገልጥ ቃል ነው። አርዮሳውያን ፈጥሮ ፈጠረበት ብለው ያልሆነ ትርጉም ከሚሰጡት ጋር ምንም ዝምድና የለውም። እግዚአብሔር አምላክ ጥንት በአበው ምሳሌ፣ በነቢያት ትንቢት፣ ኋላም በሐዋርያት ስብከት፣ እንዲሁም በሊቃውንት ትርጓሜ ሰው መሆኑን፣ ሰው የሆነበትን ምክንያት፣ ሰው የሆነበትም ምክንያት ከጥበቡ ሁሉ የሚደንቅ መሆኑን አናግሯል። "እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሆኖ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል" ተብሎ በመቅድመ ወንጌል እንደ ተጻፈው ድንቅ የሆነውን ምሥጢረ ሥጋዌ በብዙ አባቶች፣ በብዙ ምሳሌ አናግሯል።

ሥጋዌውን አምልተውና አስፍተው ካመሠጠሩት ሊቃውንት መካከል አንዱ ቅዱስ ኤራቅሊስ ነው። ሊቁ መጻሕፍተ ብሉያትንና ሐዲሳትን ተምሮ ኪስኪስ በምትባል ሀገር ሊቀ ጵጵስና ተሾሞ ኖሯል። ምሥጢረ ሥጋዌውን ሲያነሣ ከሥጋዌው የማትለየውን ድንግል ማርያምን ያነሣታል። ሰው የሆነውን አምላክ በድንግልና ፀንሳ በድንግልና መውለዷን የገለጠው በልዩ ምሥጢርና በአድናቆት ነው። "ኦ ከርሥ ዘተጽሕፈ ውስቴታ መጽሐፈ ግእዛን ለኵሉ ሰብእ" በማለት የገለጠው ብዙ ጥልቅ ምሥጢራት የተካተቱበት ነው። የያዘው ጉዳይ ብዙ ቢሆንም በዚህ ጽሑፍ መጽሐፉን፣ የመጽሐፉን ዓይነት፣ የመጽሐፉን ጸሓፊ፣ መጽሐፉ የተጻፈባትን ሠሌዳ በመጨረሻም የሊቁን አድናቆት እናቀርባለን።

## ፩.መጽሐፉ

መጽሐፍ የተባለው ሊተላለፍ የተፈለገው አሳብ ወይም መልእክት የሚገኝበት ነው። ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መልእክት የያዙትን መጻሕፍት መጻሕፍት አምላካውያት፣ መጻሕፍት ክቡራት፣ መጻሕፍት ንጹሓት በማለት ይጠሯቸዋል። ምኑናት መጻሕፍተ ዕዳ፣ መጻሕፍተ ደብዳቤ አሉና ከእነዚያ ሲለይ ክቡራት፣ ርኩሳት መጻሕፍተ ጥንቆላ አሉና ከእነዚያ ሲለይ ንጹሓት አላቸው እያሉ መንፈሳዊ ትምህርት የያዙትን መጻሕፍት ቅዱሳት በማለት ይገልጿቸዋል። በዚህ ዐውድ መጽሐፉ የተባለው እግዚአብሔር ወልድ ነው። ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም "በእርሱ ፈቃድ፣ በአባቱ ፈቃድ፣ በመንፈስ ቅዱስም ፈቃድ መጥቶ አዳነን" በማለት በውዳሴ ማርያም ዘሠሉስ እንደገለጸው ወደዚህ ዓለም የተላከው መልእክት እርሱ ነው። በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት አብ ልብ ነው፤ ወልድ ቃል ነው፤ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ነው።ስለዚህ አብ ቃሉን ላከ። የአብ ቃል ደግሞ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ ነው። ስለዚህ መጽሐፉ ወልድ ነው።

ሊቃውንቱ በትርጓሜ እንዳስረዱን ቃል በልብ ህልው ሆኖ ሲኖር ጸሓፊ ብራና ዳምጦ፣ ቀለም በጥብጦ፣ ብዕር ቀርጾ ሲጽፈው በልቡናው ህልው ሆኖ የነበረው ቃል አካል ገዝቶ ግዘፍ ነሥቶ ይገለጣል፣ ከዓይነ ሕሊና ዐልፎ ለዓይነ ሥጋም ይታያል። ቅድመ ዓለም የነበረው፣ ዓለምን የፈጠረው፣ ዓለምን አሳልፎ የሚኖረው አካላዊ ቃል በአብ ልብነት በእርሱ ቃልነት፣ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ህልው ሆኖ የነበረው ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በአጭር ቁመት፣ በጠባብ ደረት ተወስኖ ሲገለጥ በዓይን የሚታይ፣ በእጅ የሚዳሰስ ሆነ።ይህን በተመለከተ ወንጌላዊው ዮሐንስ "ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያ የነበረውንና በጆሯችን የሰማነውን፣ በዓይኖቻችንም ያየነውን፣ የተመለከትነውን እጆቻችንም የዳሰሱትን እንነግራችኋለን" (፩ኛ ዮሐ.፩፥፩) በማለት አስተማረ። ስለዚህ መጽሐፉ በሥጋ ማርያም የተገለጠው የአብ አካላዊ ቃል ነው።

ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ "እግዚአብሔር ለሕዝቡ በውስጧም ለተወለዱት አለቆችዋ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል"(መዝ.፹፯፥፮) እንዳለ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊያስተላልፈው የፈቀደውን መልእክት በመጽሐፍ ይገልጻዋል።እግዚአብሔር ፈቃዱን የገለጠበት፣ ኃይሉ፣ ሥልጣኑ የተገለጠበት እውነተኛው መጽሐፍ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የእግዚአብሔርን ሰው መሆን አምልቶና አስፍቶ የነገረን ወንጌላዊው ዮሐንስ "በአባቱ ዕቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ገለጠልን እንጂ እግዚአብሔርንስ ከቶ ያየው የለም" (ዮሐ.፩፥፲፰) በማለት አስተማረ። ራሱን እግዚአብሔርን ነቢያት በጻፉት መጽሐፍ እንዲሁም የነጻነት ደብዳቤያችን በተጻፈበት መጽሐፍ በኢየሱስ ክርስቶስ አወቅነው።

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስም "ይህም ሁሉ ነገር እንደታተመ መጽሐፍ ይሆንባቸዋል፤ ማንበብንም ለሚያውቅ ይህን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ ታትሟልና ማንበብ አልችልም ይላቸዋል። ደግሞም መጽሐፉን ማንበብ ለማያውቅ ይህን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ ማንበብ አላውቅም ይላቸዋል" (ኢሳ. ፳፱፥፲፩-፲፪) በማለት በተናገረው ትንቢት ላይ "የታተመ፣ ያልታተመ መጽሐፍ የሚለውን መተርጉማን በብዙ መልኩ የተረጐሙት ቢሆንም በዋናነት ለእመቤታችንና ለጌታችን ሰጥተው የተረጐሙትን እንመልከት።

መጽሐፉ የእመቤታችን ምሳሌ ሲሆን ማንበብ የሚያውቅ፣

ማንበብ የማያውቅ የተባለው ዮሴፍ ነው። ዮሴፍ ሚስቱን በግብር ያውቃታል፤ ድንግል ማርያምን ግን በግብር አያውቃትም። በሌላ በኩል ድንግል ማርያምን በመልክ ያውቃታል፤ በግብር ግን አያውቃትም። በግብር ሳያውቃት በድንግልና ፀንሳ በድንግልና መውለዷ እጅግ አስጨንቆታል። መጽሐፉ የጌታችን ምሳሌ ሲሆን ማንበብ የሚያውቅ ማንበብ የማያውቅ ተብለው የተገለጡት አይሁድ ናቸው። አካላዊ ቃል በሥጋ ማርያም ከእነርሱ ዘር እንደሚወለድ ትንቢት የተነገረላቸው፣ ሱባኤ የተቈጠረላቸው ናቸው። አይሁድ ትንቢት የተነገረላቸው፣ ሱባኤ የተቈጠረላቸው ሆነው ሳለ አምላክ ወልደ አምላክ በአጭር ቁመት፣ በጠባብ ደረት ተወስኖ ከእነርሱ ዘር ሲወለድ መቀበል አልቻሉም። መቀበል ባለመቻላቸውም በደረቅ ግንባር ዓይን ሲፈጥር፣ በዝግ ቤት ገብቶ ሳያዩት ሲወጣ፣ የአራት ቀን ሬሳ አልዓዛርን ሲያነሣ ተጨነቁ።

ስለዚህ ለሰው ልጅ ሁሉ የነጻነት ደብዳቤ የተጻፈበት መጽሐፍ የተባለው ዓለምን ሊያድን በአጭር ቁመት፣ በጠባብ ደረት ተወስኖ ከድንግል ማርያም የተወለደው፣ ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቈርሶ ዓለምን ያዳነው፣ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እንኪያስ እናንተ ልጆች ናችሁ እንጂ ባሮች አይደላችሁም" (ገላ.፬፥፯) በማለት የተናገረለት ነው። የዲያብሎስ ባሪያ ሆኖ የነበረው የሰው ልጅ ከባርነት ነጻ የወጣበት፤ አምላክ ወልደ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን መረዳት ይገባል።

## ፪. የመጽሐፉ ዓይነት

የጥንቆላ መጻሕፍት፣ ሳይንሳዊ መጻሕፍት፣ ልቦለድ መጻሕፍት፣ የታሪክ መጻሕፍት፣ ሌላም ሌላም መጻሕፍት ቢኖሩም ሊቁ ሊነግረን የፈለገው ግን የነጻነት ደብዳቤ የተጻፈበትን፣ ንጹሕና ቅዱስ የሆነውን  መጽሐፍ ነው። "ለሰው ሁሉ ከመገዛት የነጻነት ደብዳቤ የተጻፈባት" የሚለውን ስንመረምር በመጽሐፉ ውስጥ ያለው መልእክት ነጻነት ነው። በሠሌዳዋ ላይ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ራሱ ወልድ ሲሆን እርሱም የሰውን ሁሉ ነጻነት ያወጀ ነው።

ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስ "እግዚአብሔርን አቡነ ብለን እንጠራው ዘንድ፣ በፍዳ የተያዘንበትን የቀደመ አባታች አዳምን ትተናል" (ድርሳነ ቄርሎስ ወጸላድዮስ ምስለ ተረፈ ቄርሎስ ምዕ.፲፩ ቁ.፳-፲) በማለት የገለጠው የቀደመው አዳም በፍዳ የተያዝንበት፣ ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ከተያዝንበት ዕዳ ነጻ የወጣንበት፣ የቀደመው አዳም ሞትን ያመጣብን፣ ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሞትን ድል አድርጎ ሕይወትን ያደለን መሆኑን ያስገነዝባል። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "እንግዲህ በአንዱ ሰው በደል ዓለም ሁሉ እንደተፈረደበት፣ እንዲሁ ደግሞ በአንድ ሰው ጽድቅ ሰው ሁሉ ይጸድቃል። በአንድ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደሆኑ እንዲሁ ደግሞ በአንድ ሰው መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ" (ሮሜ ፭፥፲፰) በማለት የገለጠው አስቀድሞ የተገለጠውን የሚያጎላ ቃል ነው። ስለዚህ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከሲኦል ወደ ገነት፣ ከባርነት ወደ ነጻነት የተሸጋገርንበት እውነተኛ፣ ቅዱስና ንጹሕ የነጻነት መጽሐፍ ነው።

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም እመቤታችንን ባመሰገነበት ውዳሴው "የአዳምንና የሔዋንን የዕዳ ደብዳቤያቸውን ቀደደላቸው" በማለት የተናገረውን ሊቃውንት በትርጓሜያቸው እንደሚነግሩን አዳምና ሔዋን በፈቃዳቸው ራሳቸውን የዲያብሎስ ባሪያ አድርገው የጻፉትን የዕዳ ደብዳቤ አንዱን በሲኦል አንዱን በማየ ዮርዳኖስ ጥሎት ይኖር ነበር። ዲያብሎስ በማየ ዮርዳኖስ የጣለውን ጌታ በተጠመቀ ጊዜ፣ በሲኦል የነበረውን ደግሞ በዕለተ ዓርብ በአካለ ነፍስ ወርዶ አጥፍቶታል። ስለዚህ  የባርነት ደብዳቤያችንን ቀድዶ የነጻነት ደብዳቤያችንን ያወጀልን አካላዊ ቃል በአማናዊት ሠሌዳ በድንግል ማርያም ላይ ተቀርጾ ነውና በሊቁ አነጋገር የነጻነታችን ደብዳቤ ለተጻፈባት ማኅፀን አንክሮ ይገባል በማለት መጽሐፉ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ የነጻነት መጽሐፍ መሆኑን ገለጠልን።

## ፫. መጻፊያ ሠሌዳ

ሊተላለፍ የተፈለገው አሳብ መጽሐፍ ሲባል አሳቡ የሚሠፍርበት መጻፊያ ደግሞ  ሠሌዳ ይባላል። የኢሳይያስን ትንቢት የተረጐሙ ሊቃውንትን ትርጓሜ ስንመለከት መጽሐፏ የድንግል ማርያም ምሳሌ መሆኗን ይነግሩናል። ስለዚህ ድንግል ማርያም መጽሐፍ ትባላለች። መጽሐፍ የሚባለው ሊተላለፍ የተፈለገውን አሳብና አሳቡ የሠፈረበትን ሠሌዳ አንድ ላይ አጠቃሎ በመሆኑ መጽሐፉ የእመቤታችን ምሳሌ ሲሆን በውስጡ ያለው መልእክት ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ነው። መጽሐፉ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን ደግሞ መልእክቱ የሚሠፍረው በሠሌዳ ላይ በመሆኑ ሠሌዳዋ ድንግል ማርያም ስለሆነች በመጽሐፉ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ቃሉ የተጻፈባት ሠሌዳ ደግሞ ድንግል ማርያም ተብሎ ይገለጻል።

ድንግል ማርያም ሰማይና ምድር የማይወስነውን አካላዊ ቃል በኅቱም ድንግልና ፀንሳ በኅቱም ድንግልና የወለደች አማናዊት ሠሌዳ ናት። አባ ሕርያቆስ "ቅድስት ድንግልንም ለሁሉ ድንቅ የሚሆን የፅንሷን ነገር እንዲህ እያልን እንመርምራት፤ ድንግል ሆይ እሳተ መለኮት በሆድሽ ባደረ ጊዜ ፊቱ እሳት፣ ልብሱ እሳት፣ ቀሚሱ እሳት ነው፤ እንደምን አላቃጠለሽ? ሰባት የእሳት ነበልባል መጋረጃ በሆድሽ ውስጥ ወዴት ተዘጋጀ? ወዴትስ ተጋረደ? ከጎንሽ በቀኝ ነውን? ወይስ ከጎንሽ በግራ ነውን? ትንሽ አካል ስትሆኚ" (ቅዳሴ ማርያም) በማለት ከአእምሮ በላይ የሆነውን ምሥጢር ይገልጻል።

አካላዊ ቃል የተጻፈባት ሠሌዳ የተባለች ለድኅነተ ዓለም ምክንያት የሆነች፣ ነቢዩ ኢሳይያስ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር" (ኢሳ.፩፥፱) ብሎ የተናገረላት፣ እግዚአብሔር ዓለሙን ያድን ዘንድ በፈቀደ ጊዜ ድንቅ ምሥጢሩና ልዩ የሆነው ጥበቡ የተገለጠባት፣ አምላክን በኅቱም ድንግልና ፀንሳ በኅቱም ድንግልና የወለደች ድንግል ማርያም ናት።

## ፬. ጸሓፊው

ሥላሴ በስም፣ በግብር፣ በአካል ሦስት ሲሆኑ በሥልጣን፣ በመለኮት፣ በአገዛዝ፣ ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ በመፍጠር፣ ከመኖር ወደ አለመኖር በማሳለፍ፣ በፈቃድ እና ይህን በመሳሰለው ሁሉ አንድ ናቸው፡፡ስለዚህ መጻሕፍት በተዘረዘሩት ሁሉ አንድ ከሆኑ ብለው አብ ላከ፣ ወልድ ተላከ፣ ቢሉም በሥላሴ ዘንድ ላኪና ተላኪ አለ ማለት አይደለም፡፡በፈቃድ፣ በሥልጣን፣ በአገዛዝ በመለኮት እና በመሳሰለው ሁሉ አንድ ናቸውና፡፡በፈቃዱ ወደ ዚህ ዓለም ለመጣው ለወልድ የአብም ፈቃድ ስለሆነ አብ ላከ ይባላል፡፡ከዚህ በመነሣት የነጻነት ደብዳቤ ስለተጻፈበት መጽሐፍ ስንመለከት መጽሐፍ ካለ፣ መጻፊያ ሠሌዳና ጸሓፊ አለ ማለት ነው፡፡ስለዚህ ጸሓፊው ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድያ ልጁን በፈቃዱ ውረድ ተወለድ ያለው አብ ነው፡፡

ይህን በተመለከተ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አምልተውና አስፍተው ጽፈዋል፡፡ሊቁ ዲዮስቆሮስ "በአባቱ ፈቃድ ወረደ፣ በማርያም ዘንድ እንግዳ ሆነ፣ በንጹሕ ድንግልናዋ እግዚአብሔር ተወለደ" ብሎ አካላዊ ቃል ወደዚህ ዓለም የመጣውና በሥጋ ማርያም የተገለጠው በባሕርይ አባቱ በአብ ፈቃድ መሆኑን ነግሮናል (ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ)፡፡ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴ ማርያም "አብ ከሰማይ ሆኖ አየ፤ እንዳንቺ ያለ አላገኘም፤ ስለዚህ አንድ ልጁን ወዳንቺ ላከው፤ ካንቺም ሰው ሆነ" በማለት በረቡዕ ውዳሴ ማርያም በግልጥ ነግሮናል፡፡

ሊቁ አባ ሕርያቆስም ድንግል ማርያምን ባመሰገነበት ድርሰቱ "እግዚአብሔር አብ በሰማይ ሆኖ ምሥራቅንና ምዕራብን፣ ሰሜንንና ደቡብን፣ ዳርቻዎችንም ሁሉ በእውነት ተመለከተ፣ ተነፈሰ፤ አሸተተም፤ እንዳንቺ ያለ አላገኘም፤ የአንቺን መዓዛ ወደደ፤ ደም ግባትሽንም ወደደ፤ የሚወደውን ልጁንም ወዳንቺ ሰደደ" (ቅዳሴ ማርያም) በማለት አብን ላኪ ብሎ ይገልጸዋል፡፡እንዲሁም "ነአምን አበ ፈናዌ ከመ አብ ውእቱ በህላዌሁ፣ ወነአምን ወልደ ተፈናዌ ከመ ወልድ ውእቱ በህላዌሁ፣ ወነአምን መንፈሰ ቅዱሰ ማሕየዌ ከመ መንፈስ ቅዱስ ውእቱ በህላዌሁ፤ ሠለስቱ ስም አሐዱ እግዚአብሔር፤ የላከ አብን በአነዋወሩ አባት እንደሆነ እናምናለን፤ የተላከ ወልድንም በአነዋወሩ ወልድ እንደሆነ እናምናለን፤ ማሕየዊ መንፈስ ቅዱስንም በአነዋወሩ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እናምናለን ሦስቱ ስም አንድ እግዚአብሔር ነው በማለት ምሥጢረ ሥላሴን ልንረዳ በምንችለው መንገድ አስረዳን፡፡

በሊቃውንቱ የተነገረው ሁሉ በቅዱስ ወንጌል "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን እንዲያገኝ እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ቤዛ አድርጎ እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲህ ወዶታልና፡፡ዓለም በእርሱ ይድን ዘንድ ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዚህ ዓለም አልላከውምና" (ዮሐ.፩÷፲፮-፲፯) ተብሎ የተገለጠውን የበለጠ እንድንረዳው የሚያስችል ነው፡፡

## ፭. አንክሮ

ምሥጢረ ሥጋዌ ወይም የአምላክ ሰው መሆን ሲነሣ ከአእምሮ በላይ የሚሆነውና እጅግ የሚያስደንቀው በሰው አስተሳሰብ ይሆናል ተብለው የማይታሰቡ በርካታ ነገሮች መከናወናቸው ነው፡፡እሳት በጨርቅ አይጠቀለልም፤ ፍጡር ፈጣሪውን ማየት፣ መንካት፣ መሸከም፣ አይችልም፡፡ሊቀ ነቢያት ሙሴ ከባለሟልነቱ የተነሣ ላቀረበው ጥያቄ የተሰጠው መልስ "አይቶኝ የሚድን ሰው የለምና ፊቴን ማየት አይቻልህም" የሚል ነበር (ዘፀ.፴፫÷፳)፡፡ፈጣሬ ዓለማት እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ማርያም ሲገለጥ ግን አየነው፡፡አባ ሕርያቆስ "ግሩም ውእቱ ዘኢይደፈር፣ በኀቤነሰ ትሑት ውእቱ፤ ልዑል ውእቱ ዘኢይትረከብ በኀቤነሰ አርአያ ገብር ነሥአ፤ እሳት ውእቱ ዘኢይትገሠሥ ንሕነሰ ርኢናሁ ወገሠሥናሁ በላዕነ ወሰተይነ ምስሌሁ፤ የማይደፈር ግሩም ነው፤ በእኛ ዘንድ ግን ትሑት ነው፤ የማይገኝ ልዑል ነው፤ በእኛ ዘንድ ግን አርአያ ገብርን ነሣ፤ የማይዳሰስ እሳት ነው፤ እኛ ግን አየነው፤ ዳሰስነውም፤ ከእርሱም ጋራ በላን ጠጣን፤" (ቅዳሴ ማርያም) በማለት ነገረን፡፡

እናትነትና ድንግልና አብረው ሊሄዱ የሚችሉ ነገሮች አይደሉም፡፡ አንድ ሴት እናት ከተባለች ድንግል ልትሆን አትችልም፤ ድንግል ከሆነች ደግሞ እናት መሆን የምትችልበት ዕድል የለም፡፡በድንግል ማርያም ግን እነዚህ ሁለቱ መስተጻርራን አንድ ላይ ተገልጠዋል፡፡ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ይህን ድንቅ ምሥጢር "ኦ ዝ መንክር ልደተ አምላክ እማርያም እምቅድስት ድንግል አግመረቶ ለቃል ኢቀደሞ ዘርዕ ለልደቱ፣ ወኢአማሰነ በልደቱ ድንግልናሃ" በማለት በሐሙስ ውዳሴ ማርያም እንደ ገለጠው እንረዳለን፡፡

ልጅ ከእናቱ ሲቀድም፣ መቅደም ብቻ ሳይሆን ፈጣሪዋ ሲሆን፣ እናት ደግሞ የፈጣሪዋ ወላጅ ስትሆን ማየት ከዚህ በላይ የሚያስደንቅ ነገር የለምና ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም እንዲህ ያለውን ልዩ ምሥጢር "ኦ ለዝንቱ መንክር ልዑል ላዕለ ኵሉ ሕሊና፡፡ብእሲት ወለደቶ ለእግዚአብሔር ቃል ዘኮነ ሰብአ፡፡ድንግል ወለደቶ ለገባሪሃ፡፡ወለሊሁ ፈጠረ ወላዲቶ፡፡ወእምኔሃ ነሥአ ሥጋነ ዘውእቱ ፈጠረ" በማለት ያደንቃል (ሃ.አበ.፵፯÷፪)፡፡ስለዚህ ሊቁ ለዚህ ነገር አንክሮ ይገባል አለ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጽሑፍ ለሰው ሁሉ ነጻነትን ያወጀው መጽሐፍ ቅድመ ዓለም ዓለምን የፈጠረው፣ በኋለኛው ዘመን ዓለምን ሊያድን በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በሥጋ ማርያም የተገለጠው አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈባት ሠሌዳ ደግሞ አካላዊ ቃልን በኅቱም ድንግልና ፀንሳ በኅቱም ድንግልና የወለደች፣ ለዓለም ሁሉ ምክንያተ ድኅነት የሆነች ድንግል ማርያም ናት፡፡የመጽሐፉ ጸሓፊ ዓለም ይድን ዘንድ አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን እንዲሁ የወደደ በማለት የገለጠው የባሕርይ አባቱ አብ ነው፡፡ለዚህ ድንቅና ከአእምሮ በላይ ለሆነው ምሥጢረ ሥጋዌ፣ ነገረ ድኅነት አንክሮ፣ ምስጋና ይገባልና አስቀድሞ አምኖ መቀበል ከዚያም ይህን ላደረገ እግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ይገባል፡፡አምላካችን ከበረከተ ልደቱ ያሳትፈን፡፡አሜን!!✥

# የተቸገሩትን በመርዳት በረከትና የአእምሮ ሰላም እናግኝ

**ዲ/ን አሻግሬ አምጤ**

ሰዎች መልካም የሚያደርጉት መልካም የሚያደርጉ ሰዎችን አርአያ በማድረግ ነው። መልካም ማድረግን በተግባር የምንማረው ከወላጆቻችን፣ በቅርብ ከምናውቃቸው ሰዎች፣ ከቅዱሳን ገድል ነው። ቀደምቶቻችንን እንድናስብ የታዘዝነውም ለዚህ ነው። የተቸገሩ ወገኖቻቸውን የሚረዱ ሰዎች ለመልካም ነገር ከሚቀሰቀሱባቸው ነገሮች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

### መልካም የሠሩትን አርአያ በማድረግ

የምንኖርባትን ዓለም ጣዕም ሲቀይሩ የኖሩት ከሌሎች የተቀበሉት ሳይሆኑ የሰው ፍቅር በልጦባቸው ያላቸውን የሰጡት ናቸው።መስጠት ደስታን ሲያጎናጽፍ፣ የሰው እጅ ማየት ግን ኃፍረትን ያስይዛል። ለዚህም የሰው ፊት እሳት ነው የሚለው ብሂላችን ማሳያ ነው። ተረጂዎች ረዳነው ብለው ይሳለቁብኛል በማለት አፋቸውን ሞልተው ከመናገር ይሳቀቃሉ። ሰው ርዳታ ሲጠይቅ በትር ይዘው እንዳስፈራሩት ሁሉ አንገቱን ደፍቶ የሚሸቆጠቆጠው የሰው ፊት እሳት በመሆኑ ነው።

የተቸገሩትን መርዳት ለክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ ግዴታችን፣ ሥነ ምግባራዊ መገለጫችን በመሆኑ ከሌሎቹ ቀድመን ለተቸገሩ ወገኖቻችን ሁሉ እንደርሳለን። መልካም የምናደርገው በሌሎች ላይ የደረሰው መከራ እንዲደርስብን ስለማንፈልግ ጭምር ነው። ክርስቲያኖች ሃይማኖት ሳንለይ ለተቸገሩ ስንደርስ በአንድ በኩል ክርስቲያናዊ አስተምህሯችን ለሌሎች ይገለጣል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከምንቀበል ይልቅ በመስጠት የምንደሰት መሆናችንን በተግባር እንገልጣለን።

ለተቸገሩ ወገኖቻችን በመርዳት ለሚገለጠው በጎ ምግባር አብነት የሚሆነን በአንቀጸ ብፁዓን የተጠቀሰው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራ ላይ ወጥቶ "በመንፈስ ነዳያን የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። ዛሬ የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤ መጽናናትን ያገኛሉና። የዋሃን ብፁዓን ናቸው፤ እነርሱ ምሕረትን ያገኛሉና። ልባቸው ንጹሕ የሆነ ብፁዓን ናቸው፤ እነርሱ እግዚአብሔርን ያዩታልና። ዕርቅን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው፤ እነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና። ስለጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። በሚሰድቧችሁና በሚያሳድዷችሁ ጊዜ ስለእኔም እየዋሹ ክፉውን ሁሉ በሚናገሩባችሁ ጊዜ ብፁዓን ናችሁ። ደስ ይበላችሁ ሐሴትንም አድርጉ፤ ዋጋችሁ በሰማያት ብዙ ነውና፤ ከእናንተ አስቀድሞ የነበሩት ነቢያትንም እንዲሁ አሳድደዋቸው ነበርና" በማለት ያስተማረው ትምህርት ነው (ማቴ. ፭፥፫- ፲፪)።

ቅዱሳን ለክብር የበቁት አንቀጸ ብፁዓንን በተግባር በመግለጣቸው ነው። እኛ የፍጹማንን ሥራ መሥራት ባንችልም ክርስቲያኖች እንደ አቅማችን እንድንሠራ ተነግሮናል። ሰው ሲቸግረው ዓይተው የሚያዝኑ ክርስቲያኖች ንዑዳን ክቡራን ተብለው ተመስግነዋል። በዚህ ዘመን ወገኖቻችን አገር ለቀው ተሰደው፣ ቀያቸውን ትተው ተፈናቅለው እያየን ለእነርሱ የምናደርገው ድጋፍ ብቻ ሳይሆን ለእነርሱ ማዘናችን ንዑዳን ክቡራን እንደሚያሰኘን ቅዱስ ወንጌል ይነግረናል። በእርግጥ ለተቸገሩ ሰዎች መልካም የምናደርገው ያመስግኑኝ፣ ንዑድ ክቡር ይበሉኝ ብለን አይደለም።ሰዎችን መደገፋችን አምላካችንን ስለሚያስደስት፣ እኛም በዚህ ምድር ስንኖር አምላካችንን የሚያስደስት በጎ ምግባር መፈጸም ስላለብን ነው። የተፈጠርንለት ዓላማ ሠርተን ያገኘነውን በልተን እንድንደሰት ሳይሆን ሠርተን ካገኘነው ለሌላቸው በማካፈል እንድንኖር ነው። ይልቁንም ለተቸገሩ ወገኖቻችን በመድረስ ሕይወታቸው እንድትቀጥል፣ ዕድሜ ለንስሓ ዘመን ለፍስሓ እንዲያገኙ ስናግዛቸው ደስታችን ፍጹም ይሆናል።

ክርስቲያኖች በምንችለው ሁሉ ለተሰደዱት እንድንደርስላቸው አብነት የሚሆነን ትርጓሜ ወንጌል እኑ ቅዱስ በማለት ታሪኩን የሚነግረን አባት ነው። ቅዱሱ አባት ምሕረተ ሥጋዊንም፣ ምሕረተ ነፍሳዊንም በተግባር ገልጦ በቃል ያስተማረ ፈጽሞ ያሳየ አባት ነበር። ምሕረተ ሥጋዊ የሚባለው ቀዶ ማልበስ፣ ቆርሶ ማጉረስ፣ ቢበድሉት ማሩኝ፣ በሌሎች ሰዎች ቢበደሉ ደግሞ ይቅር ማለት ነው። ምሕረተ ነፍሳዊ የሚባለው ደግሞ በጎ መስሎት ይዞት የኖረውን ክፋውን ምግባር መክሮና አስተምሮ ወደ ትክክለኛው መንገድ ማስገባት ነው።እኑ ቅዱስ የሚባለው ደግ አባት አሕዛብና ክርስቲያኖች በሚዋሰኑባት ሀገር መካከል ኤጲስ ቆጶስነት ተሹሞ ክርስቲያኖችን ብቻ ሳይሆን የማያምኑትንም ሲያገለግል ይኖር ነበር።

አሕዛብና ክርስቲያኖች በተደጋጋሚ ጦርነት እየገጠሙ አሕዛብ ሲያይሉ ክርስቲያኖችን ማርከው ወስደው ባርያ አድርገው ሲገዟቸው ቅዱሱ ገንዘብ እየከፈለ ይመልሳቸው ነበር። እንዲህ እያደረገ ሲኖር ገንዘቡን ሰጥቶ ጨረሰ። ገንዘቡን ሰጥቶ በጨረሰበት ጊዜ አንዲት ድሃ መበለት ሄዳ ልጅዋ ስለተማረከባት ገንዘብ ከፍሎ እንዲያስፈታላት ጠየቀችው። ቅዱሱም ልጄ ሆይ ገንዘቤን ሰጥቼ ስለጨረስኩ ክርስቲያኖች እየተማረኩ እየሄዱ ለመከራ ሲዳረጉ እያየሁና ችግራቸውን እየሰማሁ ከማዝን እኔን ተክተሽ ልጅሽን አስፈች አላት። እርሷም ለልጇ ፍቅር ብላ ቅዱሱን አባት ተክታ ልጇን አስፈታታ ይዛ ሄደች።

አምላካችን ቀጥሎ ሊሠራው ለአሰበው ጉዳይ ምክንያት እንዲሆነው ቅዱሱ አባት ለባርነት ተተክቶ የሄደበት ሀገር ንጉሥ ሴት ልጁ ሞተችበት። ንጉሡ ልጁን ይወዳት ስለነበር ኀዘን ጸናበት። የንጉሡን ኀዘን የተመለከተው ቅዱስ አባትም ንጉሡ ሰምቶት የማያውቀውን "ልጅህን ባስነሣልህ ምን ታደርግልኛለህ" በማለት ጠየቀው። ንጉሡም ልጄ ከሞት ትነሣ እንጂ የመንግሥቴን

እኩሌታም ቢሆን እሰጥሃለሁ በማለት ቃል ገባለት::ቅዱሱም ይህንንስ አልፈልግም::የምፈልገው ከእኔም አስቀድሞ፣ ከእኔም በኋላ ተማርከው ሀገርህ የገቡትን ክርስቲያኖች ፈትተህ የምትሰጠኝ ከሆነ ልጅህን ላስነሣልህ አለው::ንጉሡ የተጠየቀው ነገር በጣም ቀላል ጉዳይ ስለነበረ ሳያቅማማ የቅዱሱን አባት ጥያቄ ተቀበለው::ቅዱሱም ልጁን አስነሣለት::ንጉሡም በገባው ቃል መሠረት ማርኮ የወሰዳቸውን ክርስቲያኖች ሁሉ ፈትቶ ሰጥቶት ይዟቸው ወደ ሀገሩ ተመለሰ (ተስፋ ገብረ ሥላሴ ትርጓሜ ወንጌል ዘማቴዎስ፣ ፲፱፻፹፰÷፻፲፬)::

በትርጓሜ ወንጌል የተጠቀሰው ታሪክ የሚያስገነዝበን በሃይማኖት የሚመስሉን ወገኖቻችን በደረሰባቸው ችግር ምክንያት ሀገር ለቀው ሲሰደዱ፣ በባርነት ተሸጠው አሕዛብ ይኖሩበት ወደ ነበረ ሀገር ሲሄዱ መታደግ የሚገባን መሆኑን ነው::እንደ ቅዱሱ አባት ራሳችንን አሳልፈን ለመስጠት የሚያስችል መንፈሳዊ ጥብዓት ባይኖረንም ካለን ከፍለን ለተቸገሩ ወገኖቻችን መስጠት ከሚጠበቅብን ክርስቲያናዊ ትሩፋት ትንሹ ነው::እስከ ሞት ድረስ የተቸገሩትን በመርዳት መታደግ፣ ሰውን ሁሉ መውደድ እንደሚገባን የተገለጠው ለራሳችን ከሚያስፈልገን ቀንሰን ሌሎችም እንደሚያስፈልጋቸው አምነን እንድንረዳ ነው::

## የሰማነውን በተግባር በመግለጥ

በዚህ የመከራ ዘመን  ሀገር ለቀው ለተሰደዱ፣ በችግር አሽክላ ታስረው ለሚሠቃዩ፣ ረሐብና ኀዘን ተጨምሮባቸው ለሚሠቃዩ ወገኖቻችን ያልደረስን መቼ ልንደርስላቸው ነው? የትሩፋት ተግባር ለመፈጸም የተነሡ ሰዎች ለራሳችን ይቅርብን ብለው ወገናቸውን ሲያስቀድሙ እኛ ደግሞ ቢያንስ ካለን በማካፈል ለወገን አለኝታነታችንን እናረጋግጥ::በዘመናችንም እኑ ቅዱስ እንደ ፈጸመው ያለ መልካም ተግባር በመፈጸም ላይ የሚገኙ አባቶች መኖራቸውን የሚገልጠው ብፁዕ አቡነ ቄርሎስን ጨምሮ ሌሎች ሦስት ሊቃነ ጳጳሳት የፈጸሙት ተግባር ነው::

“የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ታማሚ መሆናቸውን የማያውቅ ክርስቲያን የለም::ከአንድ ወር በፊት መድኃኒት አልቆባቸዋል ተብሎ በማኅበራዊ ብዙኃን መገናኛ ተነግሮ ስለነበር ክርስቲያኖች ሁሉ የከፋ ችግር ይገጥማቸዋል ብለው ሰግተው ነበር::ብዙም ሳይቆይ መድኃኒቱ ተገዝቶ ተሰጣቸው ተብሎ በመነገሩ ጭንቀቱ ወደ እፎይታ ተቀየረ::ስለ ብፁዕነታቸው ሰሞኑን የሰማነው ግን በጣም የሚያስገርም ተግባር ነው::ብፁዕነታቸው የሁሉ አባት ተብዬ የሚመጣልኝን መድኃኒት ለራሴ ብጠቀመው ታማሚ ልጆቼ ሲሠቃዩ ማየት ሊሆንብኝ ነው::የሁሉ አባት ተብየ ይህን ማድረግ እንዴት ይቻለኛል? የመንፈሳዊ ልጆቼን ጭንቀት ከማይ ሕመሙን ልቻለው ብለው የሚመጣላቸውን መድኃኒት ለሌሎች እየሰጡ እርሳቸው በሕመም እየተሠቃዩ መሆኑን ሰምተናል::ተግባራቸው እንደ እርሳቸው ያሉ አባቶችን ያላሳጣንን አምላክ እንድናመሰግን የሚያደርግ ነው::

የሰሜን ወሎና የከሚሴ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የሆኑት አቡነ ኤርምያስም  ክርስቲያኑንም፣ ሙስሊሙንም እያጽናኑ ለክርስቲያኑም ለሚስሊሙም ገንዘብ ሰጥተው የሚሰዱ አባት ናቸው::ገንዘብ ላጣው ሁሉ ያላቸውን እየሰጡ ለተቸገረ የሚረዱት ሃይማኖትን ምክንያት አድርገው ሳይሆን ሰው መሆንን አስቀድመው በጎ ነገር ማድረጋቸው ግሩም ያንተ ሥራ ያሰኛል::የሌሎችን መንጠቅ ባህል በሆነበት ዘመን ያለውን ሰጥቶ ባዶ እጅን መቅረት የሚያስገርም ክርስቲያናዊ ትሩፋት መሆኑን የእኒህን አባቶች ተግባር ዓይቶ መረዳት ይቻላል::

የዋግ ኽምራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ በርናባስ መከራ በበዛበት በዚህ ዘመን ሕዝባቸውን በማጽናናት፣ ሰው ሁሉ ተፋቅሮ በመኖር ተካፍሎ እንዲበላ ሲያደርጉ ከርመዋል::ለወገን መድረስ ማለትም እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ነው::ለተቸገረ ሕዝባቸው ተስፋ የሆኑትን ብፁዕ አቡነ በርባባስን፣ ለክርስቲያኑም ለሙስሊሙም ምክር ብቻ ሳይሆን ገንዘብ እየሰጡ የሚያጽናኑትን የብፁዕ አቡነ ኤርምያስን፣ የሚመጣላቸውን መድኃኒት ለባሰባቸው ሰዎች ሰጥተው በሕመም የሚሠቃዩትን የብፁዕ አቡነ ቄርሎስን፣ ሕዝቤ የሚደርስበትን መከራ አብሬው ሆኜ እቀበላለሁ ብለው የሲኖዶስን ስብሰባ አቋርጠው መሄዳቸውን የሰማነውን የአረጋዊውን የብፁዕ አቡነ አትናቴዎስን ተግባር በቃላት አሳክቶ መናገር አይቻልም::የእነዚህን አባቶች ተግባር የገለጥነመው ሌሎች የሠሩትን እየተናገርን እንድንኖር ሳይሆን እነርሱን አብነት አድርገን እንድንሠራ፣ በሰው ከመፍረድም እንድንታቀብ ነው::

## ችግረኞችን መርዳት የሚኖረው ጠቀሜታ

በጦርነትም ሆነ በሌላ ምክንያት ቀያቸውን ለቀው የተሰደዱትን፣ በልዩ ልዩ ምክንያት  ለችግር የተጋለጡትን ወገኖች የቋንቋም ሆነ የመልክአ ምድር ወሰን ሳናደርግ  ለተቸገረ ሁሉ መርዳት ከክርስቲያኖች ሁሉ የሚጠበቅ በጎ ተግባር ነው::ይህም በቅዱስ ወንጌል “እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን እንግዲህ በምን ይጣፍጣል? እንግዲህ የሚጠቅመው የለም::ሰዎች አውጥተው ይጥሉታል::በእግራቸውም ይረግጡታል እንጂ::እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤ በተራራ ላይ የተሠራች ከተማ መሰወር አይቻላትም” ተብሎ የተነገረው ለክርስቲያኖች ነው::

ክርስቲያንነታቸው አልጫውን ዓለም ማጣፈጥ፣ ጨለማውን ዓለም ማብራት ሲገባው ገብር ሀካይ እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ይገባል::የክርስቲያኖች ብርሃንነትና የምድር ጨው መሆን የሚገለጠው ሠርተው ራሳቸውን ከመቻል ዐልፈው ለሌላቸው ወገኖቻቸው ሰጥተው ችግራቸውን ማቃለል ሲችሉ፣ ሕይወታቸው እንድትቀጥል ምክንያት ሲሆኑ ነው::ገንዘብ፣ ዕውቀት፣ ጥበብም ሆነ ለተቸገሩ ሰዎች የሚያስፈልጋቸው ሌላ ነገር ያላቸው ሰዎች ለሌላቸው መስጠት ሲችሉ የክርስቲያኖች ቊጥር እንዳይቀንስ ከማድረግ በተጨማሪ ለንፉጎችም አርአያ ይሆናሉ::የተቸገሩ ሰዎችን መርዳት የሚኖረውን ጠቀሜታ በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል::የመጀመሪያው ለተረጅዎች የሚኖረው ጠቀሜታ ሲሆን ሁለተኛው ለረጅዎች የሚኖረው ጠቀሜታ ነው::

### ለተረጅው የሚኖረው ጠቀሜታ

ሰዎች ለመከራ በተጋለጡበት ዘመን የተቸገሩትን መርዳት ለተረጅዎች የሚኖረውን ጠቀሜታ በቃላት አሳክቶ ማጠናቀቅ አይቻልም። የመጀመሪያው ጠቀሜታ ተፈናቃዮችን ወይም ተጎጂዎችን ከጎናችሁ አለን በማለት ተስፋቸው እንዲለመልም ማድረጉ ነው። ዙሪያው ገደል ለሆነባቸው ወገኖቻችን ተስፋ መፈንጠቅ የሚያስገኘውን የአእምሮ ርካታ ምን ቋንቋ ይገልጠዋል? የተረጅዎችን የሕይወት መስመር ለመለወጥ የሚኖረው ጠቀሜታም ከፍተኛ ነው። ሰውን በዚህ ዓለም ከሚያጽናኑት ዋና ዋና ነገሮች አንዱ ተስፋ በመሆኑ ገንዘብ አውጥተን የሚያስፈልጋቸውን ስናሟላላቸው ብቻ ሳይሆን አይዟችሁ ብለን ስናጽናናቸው የተቸገሩ ወገኖቻችን ተስፋ ይለመልማል።

### ለረጅዎች የሚኖረው ጠቀሜታ

ለተፈናቀሉ ወገኖች ርዳታ ማድረግ ለርዳታ አድራጊዎች ከሚኖረው ጠቀሜታ ቀዳሚው "እናንተ የአባቴ ቡሩካን ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ትወርሱ ዘንድ ኑ፤ ተርቤ አብልታችሁኛልና፤ ተጠምቼም አጠጥታችሁኛልና፤ እንግዳም ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፤ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፤ ታምሜም ጎብኝታችሁኛልና" የሚለውን አምላካዊ ቃል መስማት ነው (ማቴ.፳፭፥፴፬- ፴፮)።

ለክርስቲያኖች ይህን የሚያጽናና ቃል ከመስማት በላይ ምን የሚያስደስተን ነገር አለ? ንፉግ የነበሩ ብዙ ሰዎች በተደረገላቸው መልካም ተግባር ተስበው ገንዘባቸውን ብቻ ሳይሆን ራሳቸውንም ሰጥተዋል። ይህን ለመረዳት መጽሐፈ ስንክሳርንና የቅዱሳንን ገድል ማንበብ ይገባል።




ማኅበረ ቅዱሳን ለተፈናቃዮች ድጋፍ ባደረገበት ወቅት

ተስፋቸው መለምለም ብቻ ሳይሆን ተፈናቃዮች በደረሰባቸው መከራ ምክንያት በረሐብ እንዳያልቁ ያደርጋል። ልጆቻቸው ተርበው ሲያለቅሱባቸው ተስፋ ቆርጠው አምላካቸውን እንዳይክዱና ሃይማኖታቸውን እንዳይለውጡም ያደርጋል። እየተራቡ ለማስተማር መሞከር ለራበው ሰው ሂድ እሳት ሙቅ እንደማለት ነውና። እንዲህ ብናደርግ ሳይቀበሉን ስለሚችሉ ችግር የገጠማቸው ሰዎች እንዴት ችግሩን ወደ መልካም አጋጣሚ መቀየር እንደሚችሉ፣ ሠርተው እንዲለወጡ ሊያነቃቃቸው ይችላል።ተፈናቃዮች ዕድሜ ልካቸውን በሰው ድጋፍ ላለመኖርና ሠርተው ተለውጠው ራሳቸውን በመቻል ሌሎችን እንዲረዱ ተግባራዊ ትምህርት ያገኙበታል።

የተደረገላቸው መልካም ተግባር ልቡናቸውን ነክቶት ገንዘባቸውን በመስጠት አልረካ ብለው ራሳቸውንም ዐሳልፈው የሰጡ ሰዎች ብዙ ናቸው።

በተአምረ ማርያም ታሪኩን የምናነበው ሲላን ከፍጹም ንፉግነት ወደ ፍጹም ርኅራኄ የተመለሰው ጓደኛው ስለእርሱ ለተቸገሩ ወገኖቹ ስለመጸወተለት ነበር።መልካም ማድረግ የሚገለጠው ለተቸገሩት ወገኖቻችን በመድረስ በመሆኑ የሲላን ጓደኛ ባለጸጋ ከነበረው ወዳጁ ተቀብሎ በገንዘቡ የተቸገሩትን ረዳበት። አምላካችን እግዚአብሔር ደግሞ የገንዘቡን ባለቤት ልቡና ለውጦ የተሰጠው አላረካኝም በማለት ያለውን ሁሉ ለተቸገሩት አከፋፍሎ እግዚአብሔርን ብቻ ከያዝኩ ይበቃኛል ብሎ በድህነት ኖሯል (ተአምረ ማርያም)። በዚህ ዘመን የምንገኝ ክርስቲያኖች

የተጠየቅነው ያለንን ሁሉ እንድንሰጥ ሳይሆን የምንችለውን እንድናደርግ ነው።የተቸገሩትን መርዳት ሰማያዊ ዋጋ ከማስገኘት በተጨማሪ የመንፈስ ርካታም ይሰጣል። ሌላውን ለማስተማርና ለማነቃቃት ጠቀሜታ ይኖረዋል። በቃል ብቻ ከመናገር የተግባር ሰው መሆንንና ከልብ ለተቸገሩ ማዘንንም ይገልጣል።ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተቸገሩ ሰዎችን በመርዳት ተስፋቸውን ስታለመልም ኖራለች።የድሮውን ትተን በቅርብ ያደረገችውን በአጭሩ እናቀርባለን።

## የተቸገሩትን በመርዳት ቤተ ክርስቲያን ያከናወነቻቸው ተግባራት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተቸገሩትን መርዳት የጀመረችው ዛሬ አይደለም። ባቋቋመችው ልማት ኮሚሽን በኩል ዘር፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ አካባቢ እና ሌላም ነገር ምክንያት ሳታደርግ ለሰው ልጅ ሁሉ ስትረዳ ኖራለች። ትምህርት ቤት በመክፈት፣ ለተራቡት የዕለት ምግብ በመርዳት፣ ንጹሕ የመጠጥ ውኃ እንዲያገኙ ስታደርግ ኖራለች። ሰኔ ፳፱ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም የተፈጸመውን የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ምክንያት በማድረግ በክርስቲያኖች ሞት፣ ስደት፣ መፈናቀል፣ የንብረት ዘረፋ በተፈጸመባቸው ጊዜ ቀድማ የደረሰችላቸው ቤተ ክርስቲያን ነበረች።

በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ክርስቲያኖች በመሰባሰብ በአህጉረ ስብከታቸው አማካኝነት የተጎዱ ወገኖቻቸውን በመርዳታቸው ፈራርሰው የነበሩ የክርስቲያኖች የንግድ ተቋማት እንዴት ተመልሰው እንደ ተቋቋሙ ዝዋይን፣ ሻሸመኔንና ሌሎች ከተሞችን ሄዶ ማየት ይቻላል። በወቅቱ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጀምሮ እስከ አጥቢያ ድረስ የተጎዱትን ለመርዳት በመሞከሩ የብዙ ሰዎችን ተስፋ ማለምለም ተችሏል። ባለፈው ዓመት የተቀሰቀሰውን ጦርነት ተከትሎ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ለሚገኙ ወገኖቻችን ርዳታ አድርጋለች። ልዐክ በማሰማራት ተዘግተው የነበሩ ባንኮች አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩ ለተጎጆዎች እንዲደርስ በማለት ገንዘብ ልካለች።

ኢትዮጵያውያን በተፈናቀሉ፣ ቀያቸውን ለቀው በተሰደዱ ጊዜ አንዳንድ አህጉረ ስብከት ስደተኞች በሚገኙበት ቦታ ሄደው ተፈናቃዮችን ረድተዋል። ለአብነት ያህል ሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በወሎ ለሚገኙ ተፈናቃዮች፣ ባሕር ዳር ሀገረ ስብከት በመተከል ለሚገኙ ተፈናቃዮች እና ከዋግ ኽምራ ተፈናቅለው በባሕር ዳር ለሚገኙ ወገኖቻችን ሃይማኖት፣ ቋንቋና ዘር ሳይመርጡ ርዳታ አድርገዋል።

በቤተ ክርስቲያን ሥር የተቋቋሙ ማኅበራትን፣ ክርስቲያን ባለሀብቶችን፣ ታዋቂ ግለሰቦችን በማስተባበር ወገኖቻችን ድጋፍ እንዲደረግላቸው የማድረጉ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል የሚኖርበት እኛ ተደስተን እየኖርን ወገኖቻችን በመከራ መኖር ስለሌለባቸው ነው። ችግራቸው ጊዜ የሚሰጥ ባለመሆኑ ድጋፉ በተደራጀ እና በተጠናከረ መንገድ እንዲቀጥል ማድረግ ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ በተፈናቃዮች ላይ የደረሰው ሥነ ልቡናዊ ስብራት እንዲጠገን መሥራትም ከቤተ ክርስቲያን የሚጠበቅ ተግባር ነው።

ችግሩ አሳሳቢ በመሆኑ ችግሩን አጥንቶ የሚያቀርብ፣ ለተፈናቃዮች የሚያስፈልጉ ነገሮችን የሚያሰባስብ፣ ለተጎጂዎች ወስዶ የሚያደርስ እና ተፈናቃዮች በቋሚነት ራሳቸውን የሚችሉበትን መንገድ የሚያመላክት ኮሚቴ ሰሞኑን በጠቅላይ ቤተ ክህነት መቋቋሙ መልካም ነው። ከደረሰው ችግር አንጻር የዘገየ ቢሆንም የተቋቋመው ኮሚቴ ሥራውን በቶሎ በመጀመር ለተጎጆዎች እንዲደርስላቸው ማገዝ ያስፈልጋል። የሚሰበሰበው ድጋፍ ለችግር ለተጋለጡት ወገኖቻችን ሁሉ ያለምንም ልዩነት እንዲደርስ መሥራትም ጊዜ የማይሰጠው ተግባር ነው።።

## ማኅበረ ቅዱሳን ለተጎጂዎች ያበረከተው

ማኅበረ ቅዱሳን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰጠችውን ኃላፊነት በመወጣት የወገን ደራሽነቱን በተግባር በመግለጥ ላይ መሆኑ ይታወቃል። በአገራችን በተከሠተው ችግር ምክንያት የተፈናቀሉ ወገኖቻችንን ለመርዳት ኮሚቴ በማቋቋም ለተፈናቃዮች የሚያስፈልጋቸውን ግብአት በማሰባብብ በማድረስ ላይ ነው። ለተፈናቃዮች ርዳታ ካደረሰባቸው አካባቢዎች መካከል ምሥራቅ ሐረርጌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ግልገል በለስ፣ ቻግኒ፣ ደሴ፣ ሸዋ ሮቢት፣ ደባርቅ፣ ጭና፣ እብናት፣ ወሊሶ፣ ትግራይ፣ ደብረ ብርሃን ተጠቃሽ ናቸው። ኮሚቴው ከክርስቲያኖች ያሰባሰባቸውን ግብአቶች በተጠቀሱት አካባቢዎች ለሚገኙ ተፈናቃዮች ማድረሱ ብዙ ጠቀሜታ አለው። ገንዘብ፣ እህል፣ ልብስ፣ የምግብ ማብሰያ ቁሳቁሶችን ማድረሱ ሌሎችም መልካም እንዲያደርጉ ምክንያት ይሆናል።እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ማኅበረ ቅዱሳን እንዲህ አደረገልን ብለው ተስፋቸው እንዲለመልም ያደርጋል።

በአጠቃላይ ለተፈናቃዮች ርዳታ ማድረግ የወገኖቻችን ሕይወት እንዲቀጥል ማድረጉን በመረዳት ለተግባራዊነቱ መሽቀዳደም ይገባል። ክርስቲያኖች ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን እንድረስላቸው የምንለውም ትናንት ለሰው ይተርፉ የነበሩ በመሆናቸው ነው። ሀብታም የነበሩት በቅጽበት ባዶ እጃቸውን ሲቀሩ፣ ለዘመናት የኖሩበትን ቦታ ለቀው ሲሰደዱ የሚደርስባቸውን ኀዘን በእኔ ቢደርስስ ብለን አስበን የምንችለውን ሁሉ ማድረግ ከክርስቲያኖች ሁሉ ይጠበቃል። በእንዲህ ዓይነት ያልታሰበ አደጋ ወገኖቻችን ገንዘባቸውን፣ ሕይወታቸውን፣ ዘመዶቻቸውን፣ ልጆቻቸውን ሲያጡ በቃል ከማጽናናት በተጨማሪ የሚያስፈልጋቸውን ማሟላት ከክርስቲያኖች የሚጠበቅ ሃይማኖታዊ፣ ምግባራዊና ምራላዊ ግዴታ መሆኑን መረዳት ይገባል።❖

# አርአያነት ተግቶ በመሥራት

ቢኒያም ወልዱ

የተከበራችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ባለፈው ዕትም ማስነበባችን ይታወቃል፡፡ ቀጣዩንና የመጨረሻውን ደግሞ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

የእግዚአብሔር ሰዎች በሥራቸው ጉንዳንን ይመስላሉ፡፡ የሚችሉትን ብቻ ሳይሆን መሥራት የሚኖርባቸውን ሁሉ በመሥራት ሠርተው ያገኙትን ለኔ ብቻ ይሁን ብለው አያስቀምጡትም፡፡ እንደ ኖኅ በእምነት እየሠሩ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ዓለምና ፍጥረትን በመላው ከጥፋት ይታደጋሉ፡፡ የትጉህ ሠራተኛ ምሳሌ የሆኑትን ጉንዳኖች ሥራ ከማይወዱ ሀኬተኞች ጋር እያነጻጸረ ቅዱስ መጽሐፍ "አንተ ታካች ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ፡፡ መንገድዋንም ተመልክተህ ጠቢብ ሁን፡፡ አለቃና አዛዥ ገዢም ሳይኖራት መብልዋን በበጋ ታሰናዳች፤ መኖዋንም በመከር ትሰበስባለች፤ አንተ ታካች እስከመቼ ትተኛለህ? ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሣለህ? ጥቂት ትተኛለህ፤ ጥቂትም ታንቀላፋለህ፤ ትተኛም ዘንድ ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ፤ እንግዲህ ድህነት እንደ ወንበዴ፣ ችጋርህም ሰይፍ እንደ ታጠቀ ሰው ይመጣብሃል" (ምሳ.፮፥፮-፲፩)፡፡

የትጋት ተምሳሌት ተደርገው የተጠቀሱት ጉንዳኖች ሕይወታቸውን የሚመሩበት አራት የሥራ መመሪያዎች አሏቸው፡፡ የመጀመሪያው የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት የመንገድ ርቀት፣ የወንዝ ሙላት የማያግዳቸው መሆኑ ነው፡፡ ተስፋ ሳይቆርጡ ዳገት ወጥተው፣ ቁልቁለት ወርደው ለራሳቸውና ለመንጋቸው ምግብ ይሰበስባሉ፡፡ ሁለተኛው በጋ ላይ ሆነው ምግባቸውን ለማግኘት እንዳይችሉ እንቅፋት የሚሆኑ እንደ ነፋስና ዝናብ ያሉ ክሥተቶች የሚፈጠሩበትን የክረምት ወራት ያስባሉ፡፡ስለዚህም የክረምት ምግባቸውን በበጋ ወራት ይሰበስባሉ፡፡ ሦስተኛው ምግብ በማይሰበሰብበት በክረምት ጊዜ በበጋ በሠሩት ቤታቸው ውስጥ ሆነው በበጋ የሰበሰቡትን እህል እየተመገቡ መጪውን በጋ ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ በበጋው ትጋታቸው ስለሚተማመኑም በክረምት ወራት ሌሎችን ፍጥረታት የሚያጋጥመው ችግር አይደርስባቸውም፡፡

አራተኛ ነገር ጉንዳኖች ሁል ጊዜም የሚሠሩት የሚያስፈልጋቸውን ያህል ብቻ ሳይሆን የሚችሉትን ሁሉ ነው፡፡ከእነዚህ ትጉሃን ፍጥረታት የሚፈልጉትን ለማግኘት የሚችሉትን ሁሉ ጥረት ማድረግን፤ መሥራት በሚችሉበት ምቹ ጊዜም፣ መሥራት በማይቻልበት ጊዜም የሚያስፈልገውን ጭምር ለማሟላት በሚያስችል መልኩ በትጋት መሥራትን፤ መሥራት በማይቻልበት ጊዜም በምቹው ጊዜ የሰበሰቡትን እየተጠቀሙ ምቹውን ጊዜ ተስፋ ማድረግን፤ አቅም የፈቀደውን ሁሉ በመሥራት የሚያስፈልገንን ብቻ ሳይሆን ለትውልድ እንዲተላለፍ የምንችለውን ያህል መትጋትን እንማራለን፡፡

**በጋ ላይ ሆነው ምግባቸውን ለማግኘት እንዳይችሉ እንቅፋት የሚሆኑ እንደ ነፋስና ዝናብ ያሉ ክሥተቶች የሚፈጠሩበትን የክረምት ወራት ያስባሉ።ስለዚህም የክረምት ምግባቸውን በበጋ ወራት ይሰበስባሉ።ሦስተኛው ምግብ በማይሰበሰብበት በክረምት ጊዜ በበጋ በሠሩት ቤታቸው ውስጥ ሆነው በበጋ የሰበሰቡትን እህል እየተመገቡ መጪውን በጋ ተስፋ ያደርጋሉ።በበጋው ትጋታቸው ስለሚተማመኑም በክረምት ወራት ሌሎችን ፍጥረታት የሚያጋጥመው ችግር አይደርስባቸውም።**

አዳም በመጀመሪያ ይመገብ የነበረው እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀለትን ነበር። ከዚያ ግን ሥራን ስላስተማረው እየሠራ ራሱንና ቤተሰቡን መመገብ የሚችልበትን ኃላፊነት ተቀበለ።ሥራ በሰውና በሌሎች ፍጥረታት መካከል ያለውን ልዩነት ማሳያ ነው። ቅዱስ ዳዊት በእንስሳትና በሰው መካከል ያለው ልዩነት ተግባር መሆኑን "የአንበሳ ግልገሎች ለመንጠቅ ይጮኻሉ፤ ከእግዚአብሔር ምግባቸውን ይሻሉ፤ ፀሐይ ስትወጣ ይሰበሰባሉ፤ በየዋሻቸውም ይተኛሉ፤ ሰው ወደ ተግባሩ ይሰማራል፤ እስኪመሽም ድረስ ሲሠራ ይውላል" በማለት የገለጠው መሥራት እንደሚገባ የሚያስተምር ቃል ነው (መዝ.፻፫፥፳፪)። ሰው ወደ ተግባሩ መሰማራቱ የተገለጠው ሥራ የሕይወቱ መሠረት በመሆኑ ነው።

ከገዳማውያን ከሚጠበቀው ነገር አንዱ ተግባረ እድ መሆኑ የሰው እጅ እንዳያዩ ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ ራስን ለመቻል፣ ሰይጣን ከሚያስነሣው ፈተና በመከለል ከፍጹምነት ለመድረስ ያግዛል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በማንም ላይ ሸክም ላለመሆን አብረውት የነበሩትን ክርስቲያኖች ጭምር ድንኳን እየሰፋ ማስተዳደሩ ክርስቲያኖች ሁሉ አብልጠን በመሥራት ማኅበራዊ ሕይወትን ማጣፈጥ የሚጠበቅብን መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ሰው መሥራት የሚገባውም እስከ ምሽት መሆኑ ተገልጧል። እስከ ምሽት ማለት ጉልበት እስከሚዝል መሥራት የሚገባ መሆኑን ያስረዳል። እስከ ምሽት ካልሠሩ ሥራ ፊት መሆን ይመጣል፤ የሰውን እጅም መመልከት ይከተላል።።

አበው "ቀን ለሠራዊት፣ ሌሊት ለአራዊት" በማለት እንደሚናገሩት የአንበሳ ደቦሎች ምግባቸውን ከእግዚአብሔር ሽተው ለመንጠቅ የሚወጡት በሌሊት ሲሆን ወደ መኖሪያ ዋሻቸው የሚሰበሰቡትም ፀሐይ ስትወጣ ነው። የብርሃን ልጆች የሆኑ ሰዎች ግን ምግባቸውን ሠርተው የሚያገኙ ስለሆነ ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በሥራ ተጠምደው ይውላሉ። "በእጃችሁ ሥራ ተመገቡ እንጂ ቅሚያን አትመኟት" ተብለዋልና (መቃ. ፎ፥፲፪)። ሌሎችም የተግሣጽ መጻሐፎቻችን ስለ ሥራ "ተግባር መፍታት እንቅልፍ ታመጣለች፤ የታካች ነፍስ ትራባለች" ይላሉ። ይህም ሥራ መፍታት ለድህነት መዳረጉን የሚያስገነዝብ ቃል ነው(ምሳ.፲፱፥፲፭)።

ድሃ ማድረግ ብቻ ሳይሆን አእምሮን በማደንዘዝና ሰውነትን በማፍዘዝ እርጅና እንዲመጣ፣ ሰውነትም በቀላሉ በበሽታ እንዲጠቃ ያደርጋል። ሌሎችን በመርዳት ከሚገኘው ደስታ በመራቅ ድሃ መሆኔን እያወቁ ሳይሰጡኝ ብሎ የሰው እጅ ማየትን ያስከትላል። ይህን ጉዳይ የበለጠ የሚያጎላው "ታካች ሰው በብርድ ምክንያት አያርስም፤ ስለዚህ በመከር ይለምናል"፤ "ምድርን የሚያርሳት፣ የሚቆፍራት ሰው የእህሉን ክምር ያበዛል" ተብሎ የተነገረው ይፈጸምበታል (ምሳ. ፳፣ ፬፤ ሲራ. ፳፣ ፳፰)። መጽሐፍ አለመሥራት የሚያስከትለውን ጉዳት ገልጦ መሥራት የሚያስገኘውን ጥምቅ ማሳየቱ ሳንታክት እንድንሠራ ለማትጋት ነው።

በቅዱስ ወንጌል ሲወቀስ በሚኖረው ገብር ሀካይና በአንጻሩም ሲወደስ በሚኖረው ገብር ኄር መካከል ልዩነት የተፈጠረው ወጥቶ ወርዶ በመሥራትና ባለመሥራት ነው። በተሰጠው መክሊት ሳይሠራበት የቀበረው ገብር ሀካይ መክሊቱ ተነጥቆ ለገብር ኄር የተሰጠው ሥራ ጠል በመሆኑ ነው። "ከሞተ በኋላ አይመለስምና ለሞተ ሰው ታለቅስለት ዘንድ አግባብ ነው። ከመሞቱ መኖሩ ይከፋልና፤ ለሰነፍ ሰው ግን በሕይወቱ ሳለ አልቅስለት" (ሲራ. ፳፥፲) ተብሎ የተገለጠውም ከሰዎች ጋር ስንኖር ሠርተን አርአያ እንድንሆን እንጂ የሰው እጅ እንድናይ አይደለም። ገብር ሀካይ የተወቀሰው ባለመሥራቱ ብቻ ሳይሆን ሰዎችን ሠርቶ ለመርዳት የሚመቀኝ በመሆኑ ጭምር መሆኑ የሚያስረዳን በማኅበራዊ ሕይወታችን ታካች ሆነን በእኛ ምክንያት አምላካችን እንዳይሰደብ ነው።

የማይታየው በልቡናችን ያለው፤ ለሰዎች ብቻ የተሰጠው ሃይማኖታችን የሚገለጠው በሥራ ነው። ላለው ሁሉ ይጨመርለታል ማለት መልካም መሥራት ለተሰጠው፣ ደግነትን ገንዘብ ላደረገ ሰው በረከት በበረከት ላይ ይጨመርለታል ማለት ነው። ለገብር ኄር የተደረገለትም እንዲህ ነው። ስንሠራ እግዚአብሔር ስለሚቀርበን በረከት የምናገኘውን ያህል ሥራ ፈትተን ስንቀመጥ ደግሞ ከመደኸየታችን በተጨማሪ አእምሯችን የሰይጣን ማኅደር ይሆናል። እንኳን የእኛን ልንሰጥ ቀምተን ለመብላት ያምረናል። እንዲህ ስናደርግ ደግሞ ማኅበራዊ ሕይወታችን ይናጋል።ሰላማችን ይደፈርሳል።

ቅዱስ ጳወሎስ በምእመናኑ ስንፍና እግዚአብሔርና ቤተ ክርስቲያን እንዳይሰደቡ የተሰሎንቄ ሰዎችን ‹‹ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ከፊት ይልቅ ልትበዙ፣ በጸጥታም ትኖሩ ዘንድ ልትቀኑ፣ የራሳችሁንም ጉዳይ ልትጠነቀቁ እንዳዘዝናችሁም በውጭ ባሉት ዘንድ በአገባብ እንድትመላለሱ አንዳችም እንዳያስፈልጋችሁ በእጃችሁ ልትሠሩ እንለምናችኋለን" (፩ኛ ተሰ.፬፡፲፪) በማለት የመከራቸው መሥራት ለነፍስም፣ ለሥጋም ስለሚጠቅም ነው።

የመጀመሪያዪቱ መልእክቱ ባለመተግበሯ ምክንያት በሁለተኛዪቱ መልእክቱ ‹‹ወንድሞች ሆይ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱሰ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን።እኛን እንድትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንምና በእናንተ ዘንድ በአንድስ እንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም። ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ ያለ ሥልጣን ስለሆንን አይደለም። ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና። ሥራ ከቶ ሳይሠሩ በሰው ነገር እየገቡ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና እንደ እነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን። እናንተ

ግን ወንድሞች ሆይ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ” በማለት ተናግሯል (፪ኛተሰ. ፫፡፰-፲)።

**ከገዳማውያን ከሚጠበቀው ነገር አንዱ ተግባረ እድ መሆኑ የሰው እጅ እንዳያዩ ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ ራስን ለመቻል፣ ሰይጣን ከሚያስነሣው ፈተና በመከለል ከፍጹምነት ለመድረስ ያግዛል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በማንም ላይ ሸክም ላለመሆን አብረውት የነበሩትን ክርስቲያኖች ጭምር ድንኳን እየሰፋ ማስተዳደሩ ክርስቲያኖች ሁሉ አብልጠን በመሥራት ማኅበራዊ ሕይወትን ማጣፈጥ የሚጠበቅብን መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።**

ሐዋርያው የተናገረው ቃል ምንኛ የሚያስደንቅ ነው። ሐዋርያው የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር የሚለውን ሕገ ኦሪት እያወቀ ቀንም፣ ሌሊትም ሳይታክት አገር ለአገር ተንከራትቶ ወንጌልን እያስተማረ በማስተማር የደከምኩት ይበቃኛል ሳይል በሰው ላለመክበድ ሠርቶ ተከታዮቹ እንዳይርባቸው ማድረጉ ክርስቲያኖች ጠንቃቃ መሆን እንደሚገባን የሚያስገነዝብ ነው።

የኤፌሶን ሰዎችንም “የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ፤ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም” እያለ ይመክራል (ኤፌ. ፬፥፳፰)። እግዚአብሔር ሰው የመሆኑ ዋነኛ ምክንያት ሰዎችን ለማዳንና ሠርቶ በማሳየት አርአያ ለመሆን ነው። ነቢዩ “እኛ ባሮቹ ተነሥተን እንሠራለን የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል” በማለት የተናገረው መልካም ሥራችን በእግዚአብሔር የሚደገፍ መሆኑን ያስገነዝባል (ነህ.፪፣፳)።መሥራት የሰው ተግባር ሲሆን መፈጸም ደግሞ የእግዚአብሔር ድርሻ ነው። ሥራን ያስተማረን እርሱ ቢሆንም የምንሠራው ግን ለራሳችን ስንል ነው። እርግጥ እግዚአብሔር ሥራን እንድንሠራ ያዘዘን የኛ ሥራ እርሱ ለሚያወርሰን መንግሥተ ሰማያት የሚያበቃ ዋጋ ነው ብሎ አይደለም። የተሰጠንም ሁሉ በዋጋ የሚተመን በኛ ድካም የሚሸፈንም አይደለም።

አባቶቻችን እንደሚነግሩን እኛ መልካም ሥራን ልንሠራ የሚገባን በመግቦቱ ስለሚያኖረን ለጌትነቱ ለመገዛት፣ ሥጋችንን ለነፍሳችን አስገዝተን ለማቆየትና ባሕርየ ሥጋን በትሩፋት ለመቅጣት፣ እግዚአብሔር ላደረገልን ሁሉ የፍቅር መሥዋዕት ለመሠዋት፣ የሚገብሩበት ርስት ባለቤትነቱ የጸና ነውና ለሰማያዊት ርስታችን ለመንግሥተ ሰማያት ግብር ለመክፈል ነው።ካልሠራን ለቤተ መንግሥት ግብር፤ ለቤተ ክህነትም አሥራት በኵራት ማውጣት አንችልም።በዘመናችን በቤተ ክርስቲያን ሳይቀር ልመናና ስርቆት የበዛው ቀዳሚቱን ሕግ በትጋት መሥራትን ስለዘነጋን ነው።

በየትኛውም ዓይነት የሕይወት መንገድ ብንሄድ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ የሚጠይቀን አይቴ ነበርከ፡- ወዴት ነበርክ? ምንተ ገበርከ፡- ምን ሠራህ? ብሎ ነው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍት ይገለጣሉ። ምግባራችን ሁሉ ይነበባል። ያን ጊዜም ምግባር ብቻ እንጂ ባለጠግነትም፣ ሹመትም፣ ባላባትነትም በአምላካዊ ሚዛን ዋጋ አያሰጥም። ነቢዩ ዳንኤል ንጉሡ ብልጣሶር እግዚአብሔርን የሚያሳዝን መጥፎ ድርጊት በፈጸመ ጊዜ የተገለጠለትን አስፈሪ ጽሑፍ ትርጕም “የተጻፈውም ጽሕፈት፡- ማኔ ቴቄል ፋሬስ ይላል፤ የነገሩም ፍቺ ይህ ነው፤ ማኔ ማለት እግዚአብሔር መንግሥትህን ቈጠራት ፈጸማትም ማለት ነው። ቴቄል ማለት በሚዛን ተመዘነች፤ ቀልላም ተገኘች ማለት ነው። ፋሬስ ማለት መንግሥትህ ተከፈለች ለሜዶንና ለፋርስ ሰዎችም ተሰጠች ማለት ነው” በማለት የነገረው እንዳይፈጸምብን ምክንያት ሳናበዛ የሚጠበቅብንን ሥራ ልንሠራ ይገባል (ዳን.፭፥፳፭- ፳፰)።

ነቢዩ የተረጎመውን ቃል በአንድ አባት ትእዛዝ እናጠቃለው። ‹‹ተገብሮ የማይዝ ሥራ የማይሠራ ሰው ምግብን አይመገብ፤ ጎረቤት ሆኖም ከእናንተ ጋር አይቀመጥ.... ሁል ጊዜም እርሱን ፍሩት፤ ከስንፍናውም ራቁ፤ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ሰነፎችን ይጠላልና” (ዲድ. አንቀጽ ፲፪፣ ፲፬-፲፭)። ክርስቲያኖች ሁሉ አምላካችን እግዚአብሔር ሥራ ፈትተን እንዳያገኘን እንትጋ።ሥራ እያለ በስንፍና ተቀምጠን፣ የሰይጣን መጫወቻ እንዳንሆን መትጋት ይገባናል። ለክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን ለማያምኑትም አርአያ የሚያደርግ ሥራ ለመሥራት የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን በረከት አይለየን። አሜን!!✠

# ብሔረ ብፁዓን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም

**ዲ/ን መዝገቡ ከፍያለው**

ትዕግሥትን እንደ ሸማ የለበሰው ኢዮብ “እግዚአብሔር በአንድም፣ በሌላም መንገድ ይናገራል፤ ሰው ግን አያስተውልም” በማለት እንደተናገረው አምላካችን እግዚአብሔር ለሰዎች የሚገለጥበት መንገድ ብዙ መሆኑን ያስገነዝባል (ኢዮ.፴፫፥፲፬)። እግዚአብሔር በሰዎች ዘንድ በተናቁት ወይም ግእዛን በሌላቸው ፍጥረታት እያደረ የሰውን ልጅ ይገሥጻል፤ ይመክራል። በለዓም በተሰጠው ሀብተ መርገም ሕዝበ እግዚአብሔርን ለማጥፋት በሄደ ጊዜ በተቀመጠባት አህያ ገሥጾታል።

በዕለተ ሆሣዕና ሕፃናቱ ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዳይዘምሩ ጸሐፍት ፈሪሳውያን በከለከሏቸው ጊዜ የቢታንያ ድንጋዮች የአምላካቸውን ክብር ተረድተው እንዲዘምሩ አድርጓል። ዛሬም በሰዎች ዘንድ በተናቁት ልቡናቸው ግን ንጹሓን በሆኑት እያደረ እግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን ይሠራል፤ የተሰወረውን ይገልጣል። በዚህ መልኩ ተገልጠው ዛሬ ለብዙዎች ድኅነትን ከሚሰጡ ታላላቅ ገዳማት አንዱ ጃራ ብሔረ ብፁዓን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ነው።

ገዳሙ የሚገኘው በባሌ ሀገረ ስብከት ጎሎልቻ ወረዳ ውስጥ ነው። የወረዳው ዋና ከተማ የሆነችው ጃራ ከደረሱ በኋላ በእግር ለሠላሳ ደቂቃ ተጉዘው ከተራራው እግር ሥር ይደርሳሉ።ተራራው ከግራኝ አሕመድ ወረራ በኋላ የስም ተፋልሶ ገጥሞት ‹‹የዐረብ ልጅ ተራራ›› ተብሎ ሲጠራ ቆይቷል። በአሁኑ ሰዓት ለሦስተኛ ጊዜ ስሙ ተቀይሮ ብሔረ ብፁዓን ተብሏል። ገዳሙ የሚገኘው በተራራው አናት ላይ ነው። ቤተ ክርስቲያኑ ከሚገኝበት ጋራ ለመድረስ ቢያንስ በበቅሎ ለአርባ ደቂቃ በእግር ደግሞ ከዚያ በላይ ተራራውን መውጣት ይጠበቃል።

ብሔረ ብፁዓን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም የተመሠረተውም ከግራኝ አሕመድ ወረራ በፊት እንደ ሆነ ይነገራል። ከወረራው በፊት በዚህ ስፍራ የመድኃኔ ዓለምና የጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ይገኝበት ነበር ይላሉ። ገዳሙ የተመሠረተውም የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዝሙር በሆኑት በታላቁ አቡነ አኖሬዎስ መሆኑን አባቶች ይናገራሉ።

የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዛሙርት ሀገረ ስብከት ተከፋፍለው ወንጌል ወዳልደረሰበት ለማድረስ በሄዱ ጊዜ ጻድቁ አቡነ አኖሬዎስ የደረሳቸው በዛሬው አጠራር ‹‹ባሌ›› ተብሎ የሚጠራው ሀገር ነበር። ታሪኩንም ዲያቆን ዳንኤል ክብረት “በባሌ አካባቢ ታላቁን ሥራ የሠሩት አቡነ አኖሬዎስ አስቀድመው በስደት፣ በኋላም በሀገረ ስብከትነት” ተመድበው መሆኑን አራቱ ኃያላን በተባለው መጽሐፉ ገልጧል (ዳንኤል ክብረት፣፳፻፮፥፫፻፴፫)።

ጻድቁ አቡነ አኖሬዎስ ባሌ ከደረሱ በኋላ በአካባቢው ብዙ ሰዎችን አስተምረው ወደ ቀናች መንገድ መልሰዋል፤ ብዙ አብያተ

> **አንድ ቀን ከብቶቹን ውኃ ለማጠጣት ገንዳውን ከወንዙ ዳር አስቀምጦ ውኃ ሊቀዳ ጎንበስ ሲል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተገልጻለት ‘ይህ የኔ ጸበል በመሆኑ እንዴት ጸበሌን ለከብቶች ትሰጣለህ’ ብላ ተናግራው ተሰወረች።እመቤታችን ለእረኛው የተገለጠችበት ቦታ በአሁኑ ጊዜ የእመቤታችን ጸበል የሚገኝበትና በሽተኞችን የሚፈውስበት ነው።**

ክርስቲያናት እና ገዳማትን መሥርተዋል:: ቅዱሱ አባት ከመሠረቷቸው ገዳማት መካከል ደግሞ ብሔረ ብፁዓን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም አንዱ ነው:: የገዳሙ አበ ምኔት አባ ተክለ ወልድ ገዳሙን በጎበኘሁበት ወቅት ‹‹ግራኝ አሕመድ በተነሣ ጊዜ በባሌ አካባቢ የነበሩትን ገዳማት እና አድባራት ሲያጠፋ ብሔረ ብፁዓን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳምንም አጥፍቶት” ነበር በማለት ነግረውኛል:: ቦታው ጠፍ ከሆነ በኋላ በአካባቢው ዐረቦች ሰፍረው ይኖሩበት ነበር::

ዐረቦቹ ተራራውን መውጣት መውረዱ ከአቅማቸው በላይ ስለሆነባቸው አካባቢውን ለቀው ሲሄዱ አንዱ ዐረብ ብቻ ከልጁ ጋር በተራራው ላይ መኖር ጀምሮ ነበር:: ለብዙ ዓመታት በስፍራው ከኖረ በኋላ ልጁ ሲሞትበት በተራራው ላይ ቀብሮት እርሱ ወደ ሀገሩ መመለሱ ይነገራል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአካባቢው ነዋሪ የዐረቡ ልጅ የተቀበረበት ተራራ ለማለት የተራራውን ስም ‹‹የዐረብ ልጅ›› እያሉ መጥራት ጀመሩ ይባላል::

ለመውጣት አድካሚ ከሆነው ተራራ ላይ መንጭቶ በሁለት ተከፍሎ ወደ ሜዳው የሚፈስ ወንዝ አለ:: ወንዙ ክረምት እና በጋ የማይደርቅ በመሆኑ ተራራው ሁል ጊዜ ለምለም እንደሆነ እንዲቆይ አስችሎታል:: ልምላሜው ደግሞ እንስሳትን የሚያረቡ ሰዎች ዓይኖቻቸውን እንዲጥሉበት አድርጎታል:: ጫካው ለፍየሎች፣ ሣሩም ለቀንድ ከብቶች ግጦሽ የተመቸ በመሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ከብቶቻቸውን ከተራራው ላይ ያሰማሩ ነበር:: ገዳሙ ጠፍቶ የእንስሳት ማሰማሪያ ሆኖ ከአምስት መቶ ዓመታት ላላነሰ ዘመን ኖሯል:: በዚህ ተራራ ላይ ከብቶች ቢሰማሩም ተራራው በጣም ረጅም በመሆኑ ምክንያት ከተራራው ወገብ ላይ እንኳ ለመድረስ ይደክሙ ነበር:: ተራራው በጫካ የተሸፈነ በመሆኑ እንደ ነብር፣ አንበሳ እና የመሳሰሉ የዱር አራዊትና የዱር እንስሳት ይገኙበት ነበር:: አንዳንድ ጊዜም አራዊቱ የአካባቢውን ነዋሪዎች ከብቶቻቸውን ይበሉባቸው ነበር::

በዚህ ተራራ ላይ ልቡናቸው ንጹሕ ለሆነና ለበቁ ሰዎች የሚገለጡ ስውራን ቅዱሳን መኖራቸው ይነገራል:: ተራራው በዚህ ሁኔታ ከቆየ በኋላ እግዚአብሔር ሥራ የሚሠራበት ጊዜው ሲደርስ ልደቱን ለእረኞች እንደገለጠው ሁሉ መድዓኔዓለም ክርስቶስ የቦታው ክብር በእረኞች አማካኝነት እንዲገለጽ አደረገ:: የገዳሙ አበ ምኔት አባ ተክለ ወልድ እንደ ነገሩኝ በዚህ ተራራ ላይ ከብቶችን የሚጠብቅ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረበት፣ ከብቶቹን እየጠበቀ በቀን ሰባት ጊዜ ዳዊት ያደርስ የነበረ አይቼው የሚባል እረኛ ነበር::

እረኛው ይጠብቅ የነበረው የራሱን ከብቶች አልነበረም:: እርሱ ምንም የሌለው ድኻ ስለነበር ከሰው ቤት ተቀጥሮ የቀጣሪውን ከብቶች ይጠብቅ ነበር:: ሁል ጊዜ ቀትር ሲሆን በተራራው ላይ በሚገኘው ወንዝ ከብቶቹን ውኃ ያጠጣ ነበር:: ከብቶቹን ውኃ የሚያጠጣበትን ገንዳም ይዞ ይንቀሳቀስ ነበር::

አንድ ቀን ከብቶቹን ውኃ ለማጠጣት ገንዳውን ከወንዙ ዳር አስቀምጦ ውኃ ሊቀዳ ጎንበስ ሲል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተገልጻለት ‘ይህ የኔ ጸበል በመሆኑ እንዴት ጸበሌን ለከብቶች ትሰጣለህ’ ብላ ተናግራው ተሰወረች:: እመቤታችን ለእረኛው የተገለጠችበት ቦታ በአሁኑ ጊዜ የእመቤታችን ጸበል የሚገኝበትና በሽተኞችን የሚፈውስበት ነው::እርሱም ይህስ እውነት አይደለም::

እኔ ኃጢአተኛ ነኝና እመቤቴ ማርያም ተገለጸችልኝ ብዬ ባስብ ድፍረት ይሆንብኛል ብሎ ለማንም ሳይናገር ቀረ:: በሌላ ቀንም እንዲሁ ከብቶቹን ውኃ ሊያጠጣ ገንዳውን አስቀምጦ ሊቀዳ ሲል ‘አንተ ይህ ጸበል የኔ ነው ለከብቶች አታጠጣ ብልህ እምቢ አልከኝ አይደል’ የሚል ድምፅ ሰማ:: ቀና ብሎ ቢመለከት አስተካክሎ አስቀምጦት የነበረው ገንዳ ተገልብጦ አገኘው:: እርሱም ደንግጦ ከዚያ ቦታ ውኃ ማጠጣት አቆመ:: ወደ ሌላ ቦታ ሄዶም ማጠጣት ጀመረ:: መጀመሪያ ያጠጣበት የነበረውን ቦታ ለቆ ከሄደበት ቦታም አንድ አዛውንት ተገለጾ ታየው:: አዛውንቱም ‘ይህ ቦታ የተከበረ ነውና ሰዎች ከብቶቻቸውን ወደዚህ እንዳያሰማሩ ንገራቸው’ ብሎት ተሰወረ::አሁንም እረኛው “እኔ ብናገር ማን ይሰማኛል” ብሎ ሳይናገር ቀረ:::


በሌላ ጊዜም በዚሁ ቦታ ከብቶችን እየጠበቀ እያለ መጀመሪያ ተገልጦለት የነበረው አረጋዊ አባት ዳግመኛ ተገልጾለት “አንተ ልጅ ተናገር ያልኩህን ሳትናገር ቀረህን? አሁንም ተከተለኝና ላሳይህ:: ይህ የምታየው ጫካ በሙሉ በቅዱሳን የተሞላ ነው:: ይህ ስፍራም ታላቅ ገዳም ይሆናልና እሑድ ቤተ ክርስቲያን ሄደህ ለማስቀደስ ለተሰበሰቡት ክርስቲያኖች ሁሉ ተናገር›› አለው::

እረኛውም “ጌታዬ እኔ ደካማ እና የተናቅሁ ነኝ:: አሁን አንተ የነገርከኝን ሄጄ ብናገር የሚሰማኝ የለምና በሰዎች ዘንድ ተሰሚነት ያላቸው ሰዎችን ላክ:: እኔ ለዚህ የተገባሁ አይደለሁምና የሚሰማኝ ሳይኖር ሄጄ አልናገርም›› አለው:: በአረጋዊ ተመስሎ ሲያነጋግረው የነበረውም ‹‹ና የገዳሙን ዳርቻ ላሳይህ› ብሎ ይዞ ዙርያውን አሳየው:: በዚያ ጫካ ውስጥ የሚኖሩ ቅዱሳንንም አሳየውና ‹‹መልእክቱን እንድትናገር የተመረጥከው አንተ በመሆንህነ ሄደህ ተናገር” አለው::

አይቼው የተባለው እረኛም ማታ ከብቶቹን ወደ ቤት ከአስገባ በኋላ ቅዱሳኑ ቀን የነገሩትን ለአሳዳሪው ክርስቲያን ነገረው:: ለአሳዳሪው ፍጹም ክርስቲያን ነበርና ‹‹የነገርከኝ እውነት ሊሆን ይችላል፤ ከዚህ በፊት ተራራው ገዳም ነበር እየተባለ ሲነገር እሰማ ነበር:: ስለዚህ እንደ ተነገረህ እሑድ በከተማው ውስጥ ወደሚገኘው የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሄደህ ለምእመናን ተናገር::

እኔ ታላላቅ ሽማግሌዎችንና ካህናትን ለመናገር እድል እንዲሰጡህ እነግራቸዋለሁ አለው፡፡ እረኛው አይቼውም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ንገር የተባለውን መልእክት ለምእመናን ተናገረ፡፡ ሕዝበ ክርስቲያኑም አይቼው የተናገረውን ሰምተው ተገረሙ፡፡ በአንድ ልብም እውነት ነው ብለው አመኑ፡፡ አይቼው በጫካው ውስጥ የተመለከተውን መንፈሳዊ ምሥጢር ለምእመናን የተናገረው በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ነበር፡፡

በዚያው ዓመት ሕዝበ ክርስቲያኑ ተሰብስቦ መከረ፡፡ቦታውን እንዴት ማስከበር እንደሚገባውም ተወያየ፡፡ በጥር ወርም የጥምቀትን በዓል ምክንያት በማድረግ በጃራ ከተማ በሚገኘው የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በደባልነት የነበረውን የጻድቁን የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ጽላት ይዘው ወደ ስፍራው ሄደው ጥምቀትን በዚያ ቦታ አከበሩ፡፡ ከዚያ በኋላ ስፍራውን ለማስከበር ሽማግሌዎችን መርጠው መውጣት መውረድ ጀመሩ፡፡ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ገዳሙ ዳግመኛ ተመሥርቶ ተራራው



ብሔረ ብፁዓን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን

የስውራንም፣ በገሐድ የሚታዩ ክርስቲኖችም መናኸሪያ ሆነ፡፡ ቦታውንም የባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ‹‹ብሔረ ብፁዓን›› ብለው ሰይመው ገዳም አድርገውታል፡፡ ገዳሙ በአሁኑ ሰዓት ይዞታው ተከብሮለት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ገዳም ውስጥ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም፣ የቅድስት ሐና፣ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ የቅዱስ ሚካኤል ጽበሎች ፈልቀው በሽተኞችን በመፈወስ ላይ ናቸው፡፡ ብዙ ሕሙማንም ወደ ተቀደሰው ቦታእየሄዱ ከበሽታቸው እየተፈወሱ ንስሓ ገብተው ሥጋውን ደሙን እየተቀበሉ ነው፡፡ በዚህ ገዳም ብዙ ስውራን ቅዱሳን የሚገኙ ሲሆን እግዚአብሔር ለመረጣቸው አንዳንድ ክርስቲያኖች እየተገለጡ እንደሚያነጋግሯቸውም አባቶች ይነገራሉ፡፡ ገዳሙ የአንድነት ገዳም ሲሆን በአሁኑ ሰዓት መነኮሳት እና እናቶች መነኮሳይያት ይኖሩበታል፡፡ በጽኑ ሕመም ተይዘው ወደ ተቀደሰው ገዳም ሄደው ከደዌያቸው የተፈወሱ ምእመናን እና ሕፃናት ከዚህ ገዳም አንወጣም ብለው ከመነኰሳቱ ጋር አብረው እየኖሩ መሆናቸውን በቦታው በተገኘሁ ጊዜ አረጋግጫለሁ፡፡

ገዳሙ የእርሻ ቦታ የሌለው ቢሆንም ከገበሬዎች መሬት እየተከራየ በማረስ መናንያኑ መቅኑን እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ገዳሙ እንደ ልብ ውኃ የሚገኝበት በመሆኑ ከተራራው ግርጌ የሚገኘው ቦታ ቢፈቀድለት የልማት ሥራ ሊሠራበት ይችል ነበር፡፡ነገር ግን እስካሁን ለገዳሙ የተሰጠ የእርሻ ቦታ ባለመኖሩ የመናንያኑ መቅኑን በአካባቢው ገበሬዎች እጅ ወድቋል፡፡ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መናንያኑ በጥረታቸው ወጥተው ወርደው ከገበሬዎች መሬት እየተከራዩ ማረስ በመጀመራቸው እንጂ ከጥቂት ዓመታት በፊት ለመናንያኑ መቅኑን የሚሰፍሩት በጃራ ከተማ የሚኖሩ ምእመናን እንደ ነበሩ አባቶች ይናገራሉ፡፡

የገዳሙ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ተራራማ ከመሆኑ በተጨማሪ ጫካ የበዛበት በመሆኑ ለንብ ርባታ የተመቸ ነው፡፡ሆኖም የንብ ርባታውን ለማከናወን የባለሙያ እገዛ ያስፈልጋል፡፡የንብ ርባታ ባለሙያዎች ለመናንያኑ የንብ ማነብ ሥልጠና እና ትምህርት ቢሰጧቸው ገዳሙ እንደ ልብ ማር የሚገኝበት ቦታ ይሆን ነበር፡፡ ተራራውን እያጋመሰ በሚወርደው ወንዝ የመስኖ ልማት ሥራዎች የሚሠሩበት አግባብ በባለሙያ ተጠንቶ ቢቀርብ መናንያኑ ከራሳቸው ተርፈው ለሌላው የሚበቃ ምርት ማምረት የሚችሉ መሆናቸውን የገዳሙ አበምኔት ነግረውኛል፡፡

በአጠቃላይ አምላካችን እግዚአብሔር ፍጥረቱን በፍጥረቱ እየመገበ የሚኖር በመሆኑ ለመናንያኑ የዕለት መቅኑን አላሳጣቸውም፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን "ሰው ቦታን ይቀድሳል፤ ቦታም ሰውን ይቀድሳል" በማለት የምታስተምረው በተግባር ተገልጦ የሚታይበት ቅዱስ ቦታ ነው፡፡

በጃራ ከተማ የሚኖሩ ጽኑ ክርስቲያኖች በተቀደሰው ገዳም የሚኖሩ መናንያንን በመደገፍ በረከተ ሥጋ፣ በረከተ ነፍስ ያገኛሉ፡፡ ከተቀደሰው ቦታ በረከተ ሥጋ፣ በረከተ ነፍስ ለማግኘት የፈለጉ በመላው ዓለም የተበተኑ ክርስቲያኖች ሁሉ ከቻሉ በአካል ሄደው በመሳለምና ለገዳማውያንም የሚቻላቸውን እገዛ ቢያደርጉ ገዳማውያን አይቸገሩም፡፡ በአካል መሄድ የማይችሉ ደግሞ እግዚአብሔር አምላክ በጎ ምኞታቸውን ተመልክቶ ዋጋውን እንደሚሰጣቸው አምነው በየሚገኙበት ቦታ ሆነው የሚቻላቸውን ቢያደርጉ ይጠቀማሉ፡፡ በቅዱሱ ቦታ የሚገኙ መናንያንና ስውራን በረከት ይደርብን፡፡ አሜን!!✥

# ደቀ መዝሙርነት

ዲ/ን ማለደ ዋሲሁን

የወለዱት ልጅ ማፈሪያ ሲሆን፣ ዘመድም እንደ ባዕድ ሲሆን፣ ቤተኛም እንደ ጎረቤት ሲያደርገው ለሆነበት ለዚያ ሰው ወይም ወገን የሥቃይ ምክንያት ይሆንበታል። ቤተ ክርስቲያን ብዙዎችን ልጆቿ ብታደርግም ስመ ክርስትና ይዘው ደጇን የማይረግጡ፣ ለማደግ የእናትነት ጡቷን የማይሹ፣ ከመጋቢነቷ የተለዩ በርካቶች መሆናቸው ለነገዋ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ፈተና እንደ ተደቀነባት ያሳያል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካጋጠሟት ፈተናዎች አንዱ የክርስቶስ አካል እንደ መሆኗ አጥምቃ፣ አቊርባ ልጆቿ ያደረገቻቸውን አባላቷን ከሕፃንነት እስከ አረጋዊነት በሚደረገው የዚህ ዓለም የክርስትና ጉዞ ውስጥ በነገር ሁሉ አካል ሆነው ጸንተው የመገኘታቸው ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ መግባቱ ነው። በየአጋጣሚውና በየመንደሮቻችን የምናገኛቸው በርካታ ሰዎች ክርስቲያን መሆናቸውን ቢናገሩም ክርስቲያናዊ ሕይወትን ተላብሰው ያለመገኘት፣ ያለመተባበር፣ በሥርዓት ያለመመራት፣ በአፍኣ የመባዘን፣ በለብታ ሕይወታቸውን ሲመሩ ይታያሉ። በዚህም ምክንያት በቊጥር ብዙዎች ብንሆንም አንሰን፣ ሞልተናል ስንል ጎድለን እንገኛለን። በሰንበት ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው የሚማሩት ጥቂቶች መሆናቸውን እያሰብን ከዚያ የሚበልጠውን በየደጁ የሚባዝን መንጋ እንረሳለን።

ቀደምቶቻችን በአገልግሎት የደከሙላት ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያን ከምእመናን ጋር ያላት ትስስር እየላላ ከሄደ የክርስቲያኖች ደቀ መዝሙራዊ ሕይወት ፈተና አጋጥሞታል ማለት ነው። የቤተ ክርስቲያን ዘለዓለማዊ ሕይወትና አገልግሎት መሠረቱ ሐዋርያዊ ቅብብሎሽን ጠብቆ ደቀ መዝሙርነት እየተኩ መቀጠል ነው። የነገዋ ቤተ ክርስቲያን የምትታነጸው ዛሬ አስተምራ ባፈራቻቸው፣ በምሥጢራት አትማ ባቀፈቻቸው፣ ጠርታ ክርስቲያናዊ ጣዕሟን ባቀመሰቻቸው ደቀ መዛሙርት ነው። ደቀ መዝሙርነትን የማያስፋፋ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደቀ መዝሙርነትን የማያጸኑ በመሆናቸው የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ፈተና ውስጥ ይጥላሉ። ስለዚህ ደቀ መዝሙርነት የእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት መጠበቂያና ማጠንከሪያ መሆኑን ማስገንዘብ ግዴታ ነው።

### ደቀ መዝሙርነት ምንድ ነው?

ደቀ መዝሙርነት ከመምህር የተማሩትን ወይም አታድርግ ተብለው የታዘዙትን አምኖ በመፈጸም ተከትሎ፣ መስሎ የመገኘት ሕይወት ነው። ክርስቲያኖች በአንጾኪያ ክርስቲያን ከመባላቸው በፊት ደቀ መዛሙርት ተብለው ይጠሩ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስነብበናል። ደቀ መዝሙርነት በቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር የክርስቶስ አካል መሆንን አምኖ የመሰብሰብ ሕይወት መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይነግረናል (ሐዋ. ፲፩፥፳፮)።

ደቀ መዝሙርነት ጌታችንን ክርስቶስን አምኖ፣ ታዝዞ፣ መስሎ የመገኘት ሕይወት ነው።ደቀ መዝሙርነት ክርስቶስን መስለው በቃልም በተግባርም በማስተማር ሲያገለግሉ የሚኖሩበት ሕይወት ነው። በክርስቲያናዊ ሕይወት ዐልፈው በቃላቸው፣ በግብራቸው በገድላቸው፣ በትሩፋታቸው ካስተማሩ ቅዱሳን ከሕይወታቸው ተምሮ አርአያነታቸውን መከተል ነው።

ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት በመስጠት ምእመኖቿ ቅዱሳንን አርአያ በማድረግ መንፈሳዊ ግዴታቸውን አውቀው እንዲወጡ በሚገባ ማስተማር ይኖርባታል። በዚህ ዘመን ክርስቶስ ራስ ለሆነላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ደቀ መዝሙር ለመሆን የተገባ ሆኖ ለመገኘት በሚገባ መማር ይኖርባቸዋል። ደቀ መዝሙር መሆን ማለትም ከእውነተኞቹ መምህራን በመማር ቀደምት ክርስቲያኖችን ለመምሰል፣ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተተኪ ሆኖ ለመገኘት መዘጋጀትን ያመለክታል።

ደቀ መዝሙርነት ለቤተ ክርስቲያን ታዛዥ፣ ለካህናት ረዳት፣ በመንፈሳዊ አገልግሎት ተሳታፊና ደጋፊ መሆን፣ መከራ ሲመጣም ተሳታፊ ለመሆን መቁረጥ ነው። በዚህ መንገድ ደቀ መዝሙርነት በቤተ ክርስቲያን ካልጸና የነገዋ ቤተ ክርስቲያን የሚታዘዛት ምእመን አታገኝም። ዓላማውን ተረድተው ክብረ ክህነትን የሚቀበሉ፣ በምሥጢራት አገልግሎት ንቁ ተሳታፊ የሆኑ፣ በመከራ የሚጸኑ፣ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚተጉና በነገር ሁሉ ደጋፊ ከመሆን ዐልፈው ተሳታፊ የሚሆኑ ምእመናን ማግኘት እየከበደ ይሔዳል። ይህ ከሆነ ደግሞ ኢያሱ በመምህሩና በመሪው ሙሴ፣ ጢሞቴዎስ በመምህሩ በቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተተካ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መስሎ እነሱን አህሎ የሚተካ መሪና አገልጋይ ማግኘት አይገኝም ማለት ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም፤ ፈጽሞ የተማረ ሁሉ ግን እንደ መምህሩ ይሆናል" በማለት ያስተማረው ደቀ መዝሙር መምህሩን መምሰል የሚገባው መሆኑን ለማስገነዝብ ነው (ሉቃ. ፮፥፵)።ደቀ መዝሙርነት የቀደምት አባቶቻችንን ዕውቀት፣ ጸጋ፣ ኃይል፣ ክብር ወራሽ መሆን ማለት ነው። አደራ ተቀባይ ብቻ ሳይሆን የተቀበለውን ለቀጣይ ትውልድ የሚያስተላልፍ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን ይህን የማድረግ ግዴታ አለበት።

### ቤተ ክርስቲያን ያጋጠማት ፈተና

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከውስጥና ከውጪ በታሪክ ባጋጠሟትና በሚያጋጥሟት ወቅታዊ ፈተናዎች ምክንያት አጥምቃ ደቀ መዝሙር ካደረገቻቸው መካከል በስም ክርስቲያን ቢባሉም ከቤተ ክርስቲያን በአፍኣ የሆኑ ብዙዎች ናቸው።ራሳቸው ባዝነው ትክክለኛውን መንገድ ይዘናል ብለው ምእመናንን ለማባዘን ይሞክራሉ። ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት

መዳከምና ዘመኑን በዋጀ መንገድ ምእመናንን የመያዝ ጥበብ ማጣት የመሪዎችና የካህናት ቸልተኝነት እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ።

ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነው ቤተ ክርስቲያንን የማይመስሉ፣ እናውቃታለን እያሉ ቤተ ክርስቲያንን የማያውቁ፣ ተረድተናታል ሲሉ ያልተረዷት አካላት ለአገልግሎቷ እንቅፋት ይሆናሉ። እንደ እነዚህ ዓይነት ሰዎች እንዳይበዙ መምራን ትክክለኛውን መንፈሳዊ ትምህርት ማስተማር፣ መርተው ወደ እውነት ማድረስ፣ አርአያ ሆነው መገኘት ይጠበቅባቸዋል። ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ወገኖች ከመምህራን፣ ከእውነተኛ መሪዎች፣ ምሳሌ የሚሆን ሕይወት ካላቸው ወገኖች ማስተሳሰር ይኖርባታል።ምእመናን በፍቅር የሚቀርቡት፣ በእምነት የሚቀበሉት የትሕትና መምህር ካላገኙ ቤተ ክርስቲያንን የመምሰል ዕድላቸው ይጠባል። በዚህ ምክንያት ደቀ መዝሙራዊ ሕይወታቸው የታይታ ይሆናል።

ከውጪ ደግሞ ዘመናዊ ትምህርት፣ ዓለማዊነት፣ ልዩ ልዩ ፍልስፍናዎች፣ የኑሮ ውጣ ውረድ፣ የፖለቲካ ጫና፣ ዘረኝነት፣ የመናፍቃንና የኢአማንያን ቅሰጣ ሕይወታቸውን በግብዝነት እንዲመሩ ያደርጋል። መንፈሳዊ ሕይወታቸው በመሸርሸር ደቀ መዝሙራዊ ሕይወታቸውን ያዳክማል። በዚህም ምክንያት በርካቶች ቢጠመቁም ክርስትናው ውስጥ በተግባር የሉም። በርካቶች ክርስቲያን ቢባሉም ወደ ቤተ ክርስቲያን አይቀርቡም። በርካቶች በልማድ እንጂ በዕውቀት አልታነጹም፤ የሰበካ ጉባኤ አባል ቢሆኑም ክርስትና ለማስነሣትና የሙታንን ዝክር ለማድረስ ብቻ የሚቀርቡ ብዙዎች ናቸው። እውነተኛውን ክርስቲያናዊ ሕይወት አክራሪነት ወይም ወግ አጥባቂነት አድርገው ይመለከቱታል።ካረጁ በኋላ እንጂ በውርዝውናና በጉልምስና ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን መቅረብ አይፈልጉም።ቤተ ክርስቲያን የካህን፣ የዲያቆን፣ የሰበካ ጉባኤ አባላት ወይም የሰንበት ተማሪ ብቻ ትመስላቸዋለች። በአገልጋዮች ዘንድም ከግብዝነት የጸዳ፣ ፍቅር የተሞላበት ምሳሌያዊነት፣ የአገልግሎት ተነሣሽነት ተጓድሏል።የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ይህን የምእመናን ሽሽትና የመንፈሳዊ ሕይወት መቀዛቀዝ ለማስቀረት ደቀ መዝሙርነትን ለእያንዳንዱ ምእመን ማላበስ ይጠበቅባታል።

## ምን ይደረግ?

ደቀ መዝሙርነት እንዲጠናከርና ለምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት መሠረት እንዲሆን ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቋም፣ ምእመናንም እንደ ቤተሰብ የየድርሻቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል። ቤተ ክርስቲያን በሚገባ ብታስተምርም ምእመናን ሰምተው በተግባር ካልገለጡት እውነተኛ ክርስቲያኖችን ማግኘት አይቻልም። ሁለቱም የየድርሻቸውን ሲወጡ በሃይማኖት የጸና በምግባር የጎለመሰ ትውልድ ማግኘት ይቻላል።

ከቤተ ክርስቲያን የሚጠበቅ በመንፈሳዊ ዕውቀት ምእመናንን ማነጽ፤

ደቀ መዝሙርነት የእምነት አስተምህሮን ጠንቅቆ ማወቅ፣ ያወቁትን መጠበቅና መመስከር የሚጠይቅ ሕይወት ነው። ከዚያ የተዛነፈ ሲሆን ደቀ መዝሙርነቱን ያጣል፤ መናፍቅ፣ ከሐዲ፣ ሰነፍ፣ ዝንጉ ሆኖ ይታያል። ይህ እንዳይሆን ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ቃሉን በሚገባ ማስተማር ይኖርባታል። አሥራውን መጻሕፍት በዓይነትና በደረጃ ምእመናንን ከንባብ እስከ ትርጓሜ ስልት ድረስ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማትጋት ያስፈልጋል። እዚህ ላይ ቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙሩን "ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል" በማለት የመከረንን ልብ ይሏል (፪ ኛ ጢሞ. ፫፥ ፲፭)።

መጽሐፍ ቅዱስ የዶግማም ሆነ የቀኖና መሠረት መሆኑ፣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ስታስተምር መኖሯ እየታወቀ መናፍቃን ዓይናቸውን በጨው አጥበው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን የማታስተምር አስመስለው በማቅረብ የዋሃንን ወደ አዳራሻቸው ማፍለስን ሐዋርያዊ ተግባር እንደ መፈጸም ይቈጥሩታል። እየፈጸሙት ያለውን ጥፋት ለመቀነስ በመጻሕፍት ትርጓሜ ጉባኤ ቤትም ሆነ በቅኔ ቤት የሚሰጠውን ትርጓሜ ለምእመናን በሚመጥን መንገድ በዐውደ ምሕረት ማስተማር ይገባል። በየአገልግሎታችን እየተቀመመ የገባውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምሥጢር ቀላልና ግልጽ በሆነ መንገድ ሥርዓተ ትምህርት ቀርጾ በተለያዩ መዋቅሮች ተከታታይ ትምህርት ሆኖ እንዲቀርብ ማድረግ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስን በልዩ ልዩ መንገድ የማጥናት ባህል እንዲጠናከር አጥንቶ ማቅረብ ከምሁራን ይጠበቃል።ምእመናን አውቀውትም ሳያውቁትም የሚያንጸባርቁትን ተግባራዊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሕይወት በቃል፣ በምሳሌ፣ በምሥጢር፣ በዘይቤና በመሳሰሉት አዳብረው እንዲኖሩ የተጠናከረ ተግባር መፈጸም ከቤተ ክርስቲያን ይጠበቃል፡፡፡

አገልግሎቱን በልዩ ልዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ለሰው ልጆች ሁሉ እንዲደርስ ማድረግ የሚቻልበትን መንገድ መፈለግ ከቤተ ክርስቲያን ይጠበቃል። ቅዱሳት መጻሕፍትን በዓይነትና በደረጃ ለምእመናን በማቅረብ ማስተዋወቅ፣ ማዳረስ፣ እንዲያነቡ ማበረታታት፣ እንዲማሩባቸው ማነቃቃት ደቀ መዝሙርነትን ለማጠናከር ያግዛል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ለደቀ መዝሙርነት የተገቡ እንዲሆኑ የመጻሕፍትን ምሥጢር እንዲያውቁ ያነቃቃቸው ነበር። "በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው" የተባለው ለዚህ አብነት የሚጠቀስ ነው (ሉቃ. ፳፬፥፵፭)።

ስለዚህ ወደን አክብረን የምንስመውን መጽሐፍ ቅዱስ ቃልና ምሥጢር የበለጠ በቤተ ክርስቲያን ደቀ መዝሙርነት የምንጸናበት፣ቤተ ክርስቲያንን አብዝተን የምንወድበት፣ ሌሎችን ወደ ጥዑም ቃል የምንጠራበት ሆኖ ተደራጅቶ መቅረብ ይገባዋል። ይህ ሲደረግ ደቀ መዛሙርነትን ከቤተ ክርስቲያን

ለማስኮብለል የመጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛ ሰባኪና አስተማሪ ሆኖ ለመታየት የሚሽቀዳደመውን የመናፍቃን ዓለም ባዶ ማስቀርትም ያስችላል።

መጽሐፍ ቅዱስን በልዩ ልዩ ዘዴ ለማጥናት የሚጠቅሙ የተለያዩ መጻሕፍትን በማዘጋጀትና በማሳተም፣ በድምፅና በምስል ማሰራጫት ወንጌል ላልደረሳቸው በቀላሉ እንዲደርስ ያግዛል። የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብን ማለትም ሕፃናት፣ አረጋውያን፣ ወጣቶች፣ ዓይነ ስውራን፣ መስማት የተሳናቸውን ማስተማር በእምነትም በምግባርም እንዲጸኑ ማድረግ ጊዜው የሚጠይቀው ተግባር ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ምንነት፣ ቃሉን፣ ትርጉሙን ተግባራዊ ሕይወቱን፣ ባለታሪኮችን፣ ጸሓፊዎቹን፣ በልዩ ልዩ መንገድ እንዲረዱት መሥራት አስፈላጊ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን ብቻም ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገው የተጻፉ አዋልድ መጻሕፍትንም በዓይነትና በደረጃ መጥኖ ማሥጠናት ከቤተ ክርስቲያን ይጠበቃል። የቤተ ክርስቲያን መምህራን ዋነኛ ተግባራቸው ደቀ መዛሙርትን ማፍራት፣ ማብቃት በወንበራቸው መተካት ነው። የጌታ ደቀ መዛሙርት ከመምህራቸው ከክርስቶስ እንደ ተማሩ ሁሉ እነርሱ ደግሞ የብዙዎች መምህራን ሆነዋል። አስተምረውም ብዙዎችን ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ ታዘዋል። "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" እንደ ተባለው (ማቴ.፳፰፥፲፱-፳)። በዚህም በቃላቸውም፣ በመልእክታቸውም፣ በኑሯቸውም በርካቶችን አስተምረዋል፤ ታማኝ ደቀ መዝሙር አድርገው አንጸዋል።

የአብነት መምህራን፣ ሰንበት ትምህርት ቤቶች፣ መንፈሳዊ ኮሌጆች፣ መንፈሳዊ ማኅበራት በዚህ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። አሁን እየተደረገ ካለው በመጠንና በዓይነት ጨምሮ ማስተማር ወሳኝ ነው። ሰው የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ሳይማር ቤተ ክርስቲያንን በመምሰል ደቀ መዝሙር ሊሆን አይችልም። እገሌ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ፣ አማኝ፣ ደቀ መዝሙር ነው ሲባል በነገር ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን መስሎ መገኘት አለበት።በመጻሕፍት፣ በመምህራን፣ በትምህርት ተቋማት ተምሮ አምስቱን አዕማደ ምሥጢራት፣ ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ዐውቆ ማመንና መመስከር ይገባዋል። በመሆኑም ምእመናን ለደቀ መዝሙርነት የበቁ እንዲሆኑ ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቋም ኃላፊነቷን መወጣት አለባት።✥

*ይቆየን*

**የነገዋ ቤተ ክርስቲያን የምትታነጸው ዛሬ አስተምራ ባፈራቻቸው፣ በምሥጢራት አትማ ባቀፈቻቸው፣ ጠርታ ክርስቲያናዊ ጣዕሟን ባቀመሰቻቸው ደቀ መዛሙርት ነው።ደቀ መዝሙርነትን የማያስፋፉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደቀ መዝሙርነትን የማያጸኑ በመሆናቸው የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ፈተና ውስጥ ይጥላሉ።**

# ጸልዩ

እንዳለ ደምስስ

ዳንኤል ኅዳር ፳፩ ቀን የሚከበረውን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ዓመታዊ በዓል ለማክበር በዋዜማው ወደ እንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሄደ። ተሳልሞ አጭር ጸሎት ከአደረገ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ በስተቀኝ በኩል ከሚገኘው ዕድሜ ጠገብ ዛፍ ሥር ቆም አለ። ትንሽ ቆይቶ መዝሙረ ዳዊቱን አውጥቶ ለመጸለይ ቢሞክርም የጎደለው ነገር እንዳለ እያሰበ ሕሊናው ዕረፍት እየነሣው ተቸገረ። ነገር ግን የጎደለው ነገር ምን እንደሆነ መለየት አልቻለም።

ካህናቱ ዋዜማ ቆመዋል፤ ምእመናን በጊዜ ሄደው ለጸሎት ምቹ የሆነ ቦታ እየመረጡ በመሰየም ላይ ናቸው።የምእመናን ቍጥር በመጨመሩ ወዲያ ወዲህ የሚሉት ሲበዙ የዳንኤል አለመረጋጋት እየጨመረ ሄደ። ምንነቱን ያልተረዳው ስሜት እየናጠው በመቸገሩ "ብፁዓን እለ ተንድገ ሎሙ ኃጢአቶሙ" ብሎ ለመጸለይ የጀመረውን መዝሙረ ዳዊት በአቡነ ዘበሰማያት ቋጭቶ ዛፉን ተደግፎ ተቀመጠ።

ተቀምጦ በአሳብ ማዕበል ሲናጥ ከበድ ያለ ነገር ከጀርባው ተሰማው፤ ሆኖም ግን የተሰማውን ነገር ዘወር ብሎ ምንነቱን ለማረጋገጥ አቃተው። ግራ እንደተጋባ "ዛሬ ምን ሆኛለሁ? ለምንድን ነው እንዲህ መረጋጋት ያቃተኝ? ከቤቴ የረሳሁት ነገር ይኖር ወይስ ስእለት ተስዬ ሳልከፍል ቀርቼ ይሆን?" በማለት ራሱን ጠየቀ። ነገር ግን የጭንቀቱን ምክንያት ሊደርስበት አልቻለም።

ጀርባውን እንደ ከበደው እንደ ምንም ብሎ ወደ ኋላ ዘወር ሲል የተመለከተውን ነገር ማመን አቅቶት በሕልሜ ነው ወይስ በቁሜ እየቃዠሁ አለ? ወደ ኋላው ዘወር እንዳለ ለብዙ ደቂቃ በዚያው እንደ ሐውልት ቆሞ ቀረ።

ፀጉራቸው ከተንጨባረረና ፊታቸው በጥቁር የመኪና ዘይት ከተለወሰ፣ ትክክለኛ መልካቸው ማን እንደሆነ መለየት ከማይቻል አዳፋ ሱሪና ሸሚዝ ከለበሱ፣ በአዳፋ የጨርቅ ከረጢት ምን እንደሆነ መለየት የማይቻል ነገር ካንጠለጠሉ፣ በጥቁር ዘይት የተለወሰ ቁራጭ ብርድ ልብስ ከለበሱ፣ ሽበት የቀላቀለ የተንዠረገገ ጺም ካላቸው አንድ አረጋዊ ጋር ተፋጠጠ።

ዳንኤል ሰውየውን ከተዋወቃቸው ሰባት ዓመታት ተቈጥረዋል። ሁል ጊዜ ስለ እርሳቸው ሲያስብ ነገረ ሥራቸው ሁሉ እንቆቅልሽ ይሆንበታል። ማንነታቸውን ባያውቅም ይባስ ብሎ ይናፍቁታል።ዛሬ ከሦስት ዓመት በኋላ ፊታቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ ማየቱ ነው። ቆሞ ሲመለከታቸው ቀስ በቀስ ደስ የሚል ስሜት ይሰማው ጀመር። ቆሞ እየተመለከታቸው በነበረበት ጊዜ ሳይታወቀው ፈገግ አለ።

ሰውዬው ሲመለከቱት ቆይተው ወደ ቆመበት ቦታ ሄደው "በዚህ ወቅት እንዴት ትቀመጣለህ? ተነሥተህ ተግተህ ጸልይ!!" ብለው በቍጣ ተናግረውት ወደ በሩ መንገዳቸውን ቀጠሉ።ዳንኤል በሰማው ነገር ደንግጦ መላው አካሉ በድን ስለሆነበት መጸለይ ተሳነው።በቆመበት እንደ ደነዘዘ በዓይኖቹ ብቻ ተከተላቸው።

ሰውየው መሄዳቸውን ሲያይ አእምሮው ዕረፍት አጣ።" ወደ የት ይሆን የሚሄዱት? አሁን ለምን መጡ? ለምንስ ተቆጡኝ?" የሚሉ መልስ የሌላቸው ጥያቄዎች አእምሮውን ወጥረው ያዙት። እንኳን መጽሐፉን አውጥቶ ለመጸለይ በትክክል ለማሰብ አልቻለም። ራሱን ለማረጋጋት ዘወትር እንደሚያደርገው ጋቢውን ተሸፋፍኖ፣ ጭንቅላቱን ጉልበቶቹ ላይ አስደግፎ መቆዘም እንደ ጀመረ በዚያው ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰደው።

ለምን ያህል ሰዓት እንደ ተኛ ባያስታውስም አንድ ድምፅ ቀሰቀሰው።ሰውነቱ በላብ የተጠመቀ ቢሆንም ቅልል ብሎት ነበር።"ኡ..ፍ…ፍ..ፍ…ፍ" ብሎ በረጅሙ በመተንፈስ ተንጠራርቶ ተነሣ። ላቡን በጋቢው እየጠረገ ግራ እና ቀኝ ሲያማትር በስተቀኝ በኩል አጠገቡ ቆመው ዕብድ መሳዩ ሰው በትዝብት እየተመለከቱት መሆኑን በማየቱ እንደ ገና አቀረቀረ፤ ቀና ብሎ ፊታቸውን በድጋሚ ደፍሮ ማየት አልቻለም።

"ተግተህ ጸልይ!" የሚለውን ትእዛዛቸውን ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ቢያስብም አልቻለም። መንፈሳዊ ኃይል የምናገኝበትን መፍትሔ ሳይነግሩ እንዴት ተነሥተህ ጸልይ ይባላል አለ ለራሱ።እንደ ምንም ብሎ የጀመረውን መዝሙረ ዳዊት ካቆመበት ቀጠለ።

ዳንኤል ጸሎት ማድረግ ዳገት ቢሆንበትም የጀመረውን መዝሙረ ዳዊት እንደ ምንም ጨርሶ ቀና ቢል ሰውዬው አጠገቡ አልነበሩም። እግዚአብሔር የላካቸው ሰው ይሆኑ እንዴ ብሎ ካሰበ በኋላ አሳቡን ለመቀበል ተቸገረ። ከዚያ ይልቅ "እኚህ ሰው ማን ናቸው? ከእኔ ምንድ ነው የሚፈልጉት? ለምንድ ነው የሚከታተሉኝ? እኔስ ለምንድ ነው የምከታተላቸው? የሚሉ ጥቂዎች ተፈራረቁበት።

ዳንኤል ደገመና "ለሰባት ዓመታት ሳውቃቸው ከጥቂት ቃላት በስተቀር ተናግረውኝ አያውቁም። እውነት እኚህ ሰው ማን ናቸው? ባገኘኋቸው ቍጥር 'ጸልይ!' ብቻ ለምን ይሉኛል?" እያለ እንቆቅልሽ የሆነበትን ጉዳይ ለማወቅ ሞከረ፤ ግን አልቻለም።

ከሰባት ዓመት በፊት ዳንኤል ሰውየውን ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኛቸው አምስት ኪሎ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ከቤተ ልሔም አጠገብ ከሚገኘው ዛፍ ሥር ነበር። ከዚያ ጀምሮ አለባበሳቸውም ሆነ ቁመናቸው አልተለወጠም።

በወቅቱ ችግረኛ መስለውት ከኪሱ ገንዘብ አውጥቶ ሰጥቷቸው ነበር። እርሳቸው ግን የተቀበሉትን ገንዘብ አጠገባቸው ለነበሩ ድሆች ሰጧቸው።ሁኔታው አስገርሞት እንዴት ራሱ ድሃ የሆነ ሰው የተሰጠውን ለሌላ ይሰጣል ብሎ ይከታተላቸው ጀመር።

ዳንኤል ሁል ጊዜ የሚያስገርመው ምስካየ ኀዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ወር በገባ በ፳፯፣ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ወር በገባ በ፯፣ በዓለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን ወር በገባ በ፳፱፣ በዓታ ለማርያም ገዳም ወር በገባ በ፳ እና መንበረ መንግሥት ግቢ ገብርኤል ወር በገባ በ፲፱ ሰውየውን አለማጣቱ ነው።"ጸልዩ" ከማለት ውጪ ተጨማሪ ቃል አይናገሩም።አንድ ቦታ ላይ ቆመው እየደጋገሙ "ጸልዩ፣ ጸልዩ፣ ጸልዩ ..." ይላሉ።ዳንኤል የሰውየውን ንግግር እየሰማ ይሰሙት ይመስል ደጋግሞ "ካለ መንፈሳዊ አቅም እንዴት መጸለይ ይቻላል" ይላል።

ዳንኤል ከነበሩት ልብሶች ይሆናቸዋል ያላቸውን መራርጦ የጥር ሥላሴ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እንደሚያገኛቸው አምኖ ይዞላቸው ሄደ። በተለመደው ቦታ ከዛፉ ሥር ቆመው "ጸልዩ" ሲሉ አገኛቸው። የያዘውን ልብስ ሲሰጣቸው ከአንደበታቸው ምስጋና፣ ከፊታቸውም ደስታ ሳያሳዩ ተቀበሉት።

ታቦት ከገባ በኋላ ዳንኤል ወደ ቤቱ ሊሄድ ጉዞ ሲጀምር ዕብድ መሳዩ ሰው የተሰጧቸውን አልባሳት ለድሆች ሲያከፋፍሉ በመመልከቱ በጣም ተገረመ። እንደገና ወደ ኋላ መለስ ብሎ በዛፎቹ ተከልሎ የሚያደርጉትን መመልከት ጀመረ። ልብሶቹን አከፋፍለው ሲጨርሱ ዘወትር ከሚያንጠለጥሏት አሮጌ ከረጢት ሳንቲም አውጥተው እየዞሩ ለድሆቹ መስጠት ጀመሩ። ዳንኤልም "እኚህ ሰው ማን ናቸው?" በማለት የማይመልሰውን ጥያቄ ራሱን ጠየቀ።

ሰውዬው ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙት ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት እስከ ቀኑ አምስት ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።ብዙዎች የሚያውቋቸው በዕብደታቸው ነው።በተለይ እናቶች ባዩአቸው ቁጥር ከንፈራቸውን መምጠጥ፣ ለነፍሳቸው ያደሩ ደግሞ የሚበሉትን፣ የሚለብሱትን፣ በአጠቃላይም ይሆናቸዋል የሚሉትን ይዘውላቸው መሄድ የተለመደ ተግባራቸው ነው። እርሳቸው ግን የተቀበሉትን ለድሆች ይመጸውቱታል።ለዳንኤል እንቆቅልሽ የሚሆንበትም ይህ ድርጊታቸው ነው።"እርሳቸው የሚያደርጉትን እንድፈጽም በተግባር እያሳየኝ ይሆን" ይላል ደጋግሞ።

ምን ብሎ እንደሚጠይቃቸው ባያውቅም ምስካየ ኀዙናን መድኃኔዓለም ገዳም በአገኛቸው አንድ ዕለት ሊጠይቃቸው አሰበ። በርቀት ሲመለከቱት የሞቀ ፈገግታ የሰጡት መሰለው። ፈገግታቸው ብርታት ስለሰጠው ቀርቦ "አንድ ነገር ልጠይቅዎ ፈልጌ ነበር" አላቸው።እርሳቸውም የሚጠይቃቸውን አስቀድመው ያወቁ ይመስል ብዙም ትኩረት ሳይሰጡት "ምን ፈለግህ?" አሉት።

እርሱም "እርስዎ ግን ማን ነዎት?" አለ ማንነታቸውን ለማወቅ እየጓጓ።እርሳቸውም መልሰው "ምን ያደርግልሃል? እንኳን ስለ እኔ ስለ ራስህም አታውቅ። ወደ ፊትም በፍጹም ስለ ሌሎች ለማወቅ አትሞክር። ከአንተ የሚጠበቀው ወደዚህ ምድር የመጣህበትን ዓላማ መፈጸም ነው። ስለ ሌሎች ምን አግብቶህ ትመረምራለህ?" አሉ ቆጣ ብለው።

ዳንኤል ደንግጦና በአጠያየቁ አፍሮ አቀርቅሮ እንደ ቆመ ትተውት ከገዳሙ ወጡ። እርሱም ወደ መጣበት ተመለሰ። ለታላላቅ ክርስቲያኖች ሲያማክራቸው እንዴት ተብሎ ይጠየቅ እንደ ነበር ነገሩት። ሰውየውን ሲያውቃቸው ብዙ አይናገሩም። "እውነታቸውን ነው እኔ ምን አገባኝ? ስለ እርሳቸው ምን አመራመረኝ?" ቢልም ልቡናው ከእርሳቸው ርቆ አይሄድም።

ዛሬ ደግሞ ጠዋት ቅዳሴ እንደ ተጠናቀቀ የዳንኤል ዓይኖች ሰውዬውን በናፍቆት ማሠሣቸውን ቀጥለዋል። ነገር ግን ከንቱ ድካም ሆነበት። "ለምንድ ነው እኝህን ሰውዬ በሕይወቴ ውስጥ ያስገባሁት? እውነታቸውን ነው እንኳን ስለ ሌሎች ስለ ራሴም አላውቅም! እዚህ የመጣሁት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በረከት ለማግኘት ነው። ለምን ስለ ሰውዬው እጨነቃለሁ?" አለ የራሱ ድርጊት እያበሳጨው። ዝማሬው ቀጥሏል፣ ድፍን የአዲስ አበባ ሕዝብ እንጦጦ ማርያም የሄደ ይመስላል። ግቢው በምእመናን ተጨናንቆ መላወሻ የለም።

ዳንኤል ሊረሳቸው ስላልቻለ ዘወር ዘወር እያለ መቃኘቱን አላቋረጠም። በዚህ መካከል ድንገት በአጠገቡ ከቆሙ አንድ ሰው ላይ ዓይኖቹ ተተክለው ቀሩ። የሚያውቃቸው ቢመስለውም ስለተጠራጠረ ደጋግሞ ተመለከታቸው። ሳይታወቀው እንዴ ብሎ ተናገረ። ሰውየው ናቸው። ሲፈልጋቸው የነበሩት ሰውዬ ነጭ ለብሰው፣ ቅዱስ ቊርባን ተቀብለው አፋቸውን በነጭ መሐረብ ሸፍነው አጠገቡ ቆመዋል።

ቅዳሴ አልቆ ሁሉም ወደየመጣበት መበተን ሲጀምር ዳንኤል "የሰውየውን መጨረሻ ሳላይ ልቤ አያርፍም" ብሎ ተከተላቸው።ወደ እንጦጦ ማርያም ጸበል አቅጣጫ ሲያመሩ በቅርብ ርቀት ተከተላቸው። ከገደላማው ስፍራ ሲደርሱ ሰማይ ይውጡ፣ መሬት ይግቡ ተሰወሩበት። ዳንኤል ቆሞ ሲያስብ ቆይቶ መድፌ የጠፋበት ይመስል አካባቢውን ሲያሥሥ ወደ ጥልቅ ዋሻ የሚያስገባ በር አገኘ። ወደ ጨለማው ዋሻ ቢገባ ሊገጥመው የሚችለውን ነገር አስቦ ላለመግባት ካሰበ በኋላ ስጨነቅ አልኖርም ብሎ ጠጋ አለ። ቀረብ ብሎ ቢያዳምጥ ምንም ነገር የለም።

የአካባቢው ጭር ማለት ፍርሃት ለቀቀበት። በፍርሃትና በድፍረት መካከል እየወላወለ ጥቂት ጊዜ ቆየ። ራሱን አደፋፍሮ ወደ ውስጥ ገባ ሲል ሁለት የተዘጉ በሮች ተመለከተ። በየትኛው ልግባ እያለ ሲያወላውል ቆይቶ አንዱን ማንኳኳት እንዳለበት ወስኖ ተጠግቶ በጥቂቱ አንኳኳ። ሦስት ጊዜ እንዳንኳኳ በሩ በጥቂቱ ተከፈተ።

"ግባ!" የሚል ድምፅ የሰማ መስሎት በሩን ከፍቶ ገባ።ከውጭ ጨለማ የነበረው ከውስጥ ብርሃን ነበር። ከብርሃኑ ማዶ የተመለከተው ነገር አፍዝዞ አስቀረው። ሰውዬው እንደ ፀሐይ የሚያበሩ ብዙ ሰዎች መካከል ቆመዋል። ዳንኤልን በዝምታ ሲያስተውሉት ቆይተው ወደ ቆሙበት እንዲሄድ በእጃቸው ጠቀሱት። እርሱ ግን መንቀሳቀስ አልቻለም።

አይዞህ አትፍራ የሚል ድምፅ ሲሰማ ፍርሃቱ ከላዩ ላይ በኖ ጠፋ። በስተምሥራቅ አቅጣጫ የምስለ ፍቁር ወልዳ

ሥዕል ይታያል፣ ከሥዕሉ ግርጌ ከሃያ የማያንሱ መጻሕፍት ተደርድረዋል፣ ዘወትር የማይለያቸው ከረጢት ከአንድ ጥግ ተቀምጧል፤ በስተምዕራብ ግድግዳው ላይ "ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ሀገራችሁ ጸልዩ። በፍጹም ተስፋ አትቁረጡ!" የሚል ጽሑፍ ይነበባል።

ዳንኤል በተመለከተው ነገር ፈዝዞ እንደ ቆመ አይዞህ ወደዚህ ቅረብ አሉት። እርሱ መንቀሳቀስ ስላልቻለ ሰውየው ወደ እርሱ ቀርበው እጁን ይዘው ወደ አባቶች አቀረቡት። በቦታው የነበሩ ሰዎችን ግርማ መቋቋም ስላልቻለ መሬት ላይ ወደቀ።እንደ ወደቀ አባቶች ጸሎት እያደረጉለት መሆኑን የተረዳው ከሰመመኑ ሲነቃ ነበር። ሲነቃ አዲስ ሰው ሆኗል። አይዞህ ተነሥ ብለው ከሁላቸውም በዕድሜ አረጋዊ የሆኑ አባት መስቀል አሳለሙት። ከዚያ በኋላ ለጥቂት ጊዜ በሕልም ዓለም ይሆን በእውኑ ማስታወስ ተስኖት በደስታ ሰክሮ ቆየ።

**ታቦት ከገባ በኋላ ዳንኤል ወደ ቤቱ ሊሄድ ጉዞ ሲጀምር ዕብድ መሳዩ ሰው የተሰጧቸውን አልባሳት ለድሆች ሲያከፋፍሉ በመመልከቱ በጣም ተገረመ። እንደገና ወደ ኋላ መለስ ብሎ በዛፎቹ ተከልሎ የሚያደርጉትን መመልከት ጀመረ። ልብሶቹን አከፋፍለው ሲጨርሱ ዘወትር ከሚያንጠለጥሏት አሮጌ ከረጢት ሳንቲም አውጥተው እየዞሩ ለድሆቹ መስጠት ጀመሩ።**

ከዋሻው ከመውጣቱ በፊት የሚቀመስ ነገር ሰጡት። ጣዕሙ ቀምሶት የማያውቀው አዲስ ነገር ሆነበት። ዳንኤል ከዚያ በኋላ ዳግም የሚርበው አልመሰለውም። የማያውቀው አዲስ የደስታ ስሜት ውስጥ እንዳለ ጸሎት አድርገውለት ሊወጣ ሲል የቆመበት ቦታ ድንጋይ መሆኑን ተረዳ። ያ ሁሉ ነገር የት ገባ? እያለ ሲያሰላስል ሰውየው ለተወሰኑ ደቂቃዎ ዐረፍ የሚሉበትን ቦታ ተመለከተ።

ሰውየው ዳንኤልን ወደሀ አይደለም የተጨነቅኸው። እግዚአብሔር ምክንያት ስላለው ነው። ደግሜ አንድ ነገር ልንገርህ። ስለ ሌላ ሰው አትመራመር፤ ራስህን ፈልገህ አግኝ። ወደዚህ ምድር የመጣሁት ለምንድ ነው? ብለህ ራስህን ጠይቅ። መልሱን የምታገኘው ግን ከሰው ወይም ከራስህ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነው። ለሌላ እንቅፋት አትሁን" በማለት ዘወትር ከሚይዙት የጨርቅ ከረጢት ውስጥ አንድ መጽሐፍ አውጥተው "እንካ ይህ ለአንተ የተፈቀደ ነው" ብለው ሰጡት።

የተደጎሰ የብራና መጽሐፈ አርጋኖን ነበር። "እግዚአብሔር ለአንተ ያዘጋጀልህ ነው" አሉት። ሰውዬው ዛሬ ሌላ የማያውቃቸው ሰው ሆኑበት። ቍጡነት አይታይባቸውም። በጣም ተረጋግተው ሲናገሩ ልብን ይበረብራሉ።

ያየውና የሰማው ከአቅሙ በላይ ሆኖበት መጽሐፉን ተቀበለ። "ከመሄድህ በፊት አንድ ነገር ታደርጋለህ።" ወደ መጻሕፍቱ እየጠቆሙ "እነዚህን መጻሕፍት ለአንድ አባት ትሰጥልኛለህ። እመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ዛፉ ሥር የሚጠብቁህ ሰው ታገኛለህ" ብለው ከከረጢቱ ውስጥ ሌላ የተጣጠፈ ከረጢት አውጥተው "ይህን ለሚጠብቅህ አባት ስጥተህ ለተቸገሩ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ስጥልኝ ብሎለውሃል በላቸው። ስጥተሃቸው ተመልሰህ እስከምትመጣ የጸሎት መጻሕፍትህ እዚሁ ይቆዩህ" አሉት።

ዳንኤል የሰጡትን መጻሕፍት ይዞ ከበዓታቸው ወጣ። ከቤተ ክርስቲያን ሲደርስ "ሰላም ለኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አምሳለ ኢየሩሳሌም" ካለ በኋላ ወደ ውስጥ ገብቶ የሚፈልጋቸውን ሰው ያውቃቸው ይመስል ግቢውን ማሠሥ ጀመረ። በምሥራቅ በኩል ቢጫ የለበሱና አስኬማ ያደረጉ አንድ አባት ከዛፉ ሥር ቆመው ታዩት።

ሳያመነታ ወደ እርሳቸው ሄደ። እርሳቸውም በዓይናቸው እየተከተሉት እንደሆነ ስላስተዋለ የያዘውን መጽሐፍና የተነገረውን ቃል አድርሶ በፍጥነት ተመለሰ። ከዋሻው በር ሲደርስ ቢጫ የለበሱ ሁለት መነኵሳት በር ላይ ቆመዋል።

ዳንኤል ወደ ውስጥ ሊገባ ሲሞክር በሩ ተዘግቷል።መነኵሳቱ የደከሙ ክርስቲያኖችን እያበረታታ በሃይማኖት እንዲያጸና መክረውት፣ መጻሕፍቱንና ሰውየው እንዲሰጡት ልከውለት የነበረውን የተጣጠፈ ወረቀት ተቀብሎ ከዋሻው ወጣ። አዲስ ብርታት አግኝቷል።

ዳንኤል ወደ ቤቱ የሄደው በወረቀቱ ጽፈውለት የነበረውን መልእክት እያነበበ ነበር። "ወደ መከራ እንዳትገባ ተግተህ ጸልይ፤ መከራ ቢበዛብህም ተስፋ አትቁረጥ! ከአሁን በኋላ አንተ ሳትፈልገኝ እኔ በፈለግሁት ጊዜ አገኝሃለሁ" ይላል። ደስ አለው። ዳንኤል የተቀበለውን አርጋኖን ደጋግሞ እየሳመ "እውነትም ተግተን የምንጸልይበት ጊዜ" በማለት ለራሱ ተናገረ።✤

ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን

“አባትህን ጠይቅ ይነግርህማል፤ ሽማግሌዎችህን ጠይቅ ይተርኩልህማል” (ዘዳ.፴፪፥፯) እንደ ተባለው በጥያቄዎቻችሁ መልስ ዐምዳችን ከነገረ ሥጋዌ ጋር በተያዘ የሚነሡትን ጥያቄዎች ይመልሱልን ዘንድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ



መልአከ ታቦር ኀይለ ኢየሱስ ፋንታሁን

ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የየረር መካነ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የትርጓሜ መጻሕፍት መምህርና በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን መደበኛ አገልጋይ የሆኑትን መልአከ ታቦር ኀይለ ኢየሱስ ፋንታሁንን ጋብዘናቸዋል፡፡ እርሳቸው ፈቃደኛ ሆነው ከእኛ ጋር ያደረጉትን ቆይታም እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

**ሐመር፡- በመጀመሪያ ጥሪያችንን አክብረው ለምናነሣቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነው ስለተገኙልን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን፡፡**

**መልአከ ታቦር ኀይለ ኢየሱስ ፋንታሁን፡-** እኔም ለዚህ መርሐ ግብር ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

**ሐመር፡- መምህር በዚህ ዕትም ትኩረት ያደረግነው ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ ነው፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች ምሥጢረ ሥጋዌ ማለት ምንድን ነው? ብለው ይጠይቃሉና ትርጒሙ ምን ማለት ነው?**

**መልአከ ታቦር ኀይለ ኢየሱስ ፋንታሁን፡-** ቤተ ክርስቲያን አዕማደ ምሥጢራት የምትላቸው አሉ፡፡ እነዚህም አምስት ሲሆኑ ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት መካከል በቅደም ተከተል ሲቀመጥ ማለትም ምሥጢረ ሥላሴ ካልን በኋላ በሁለተኛ ደረጃ የሚገኘው ምሥጢረ ሥጋዌ ነው፡፡ ምሥጢረ ሥጋዌ ሲባል በቀጥተኛ ትርጒሙ ሰው የመሆን ምሥጢር ተብሎ ይተረጎማል፡፡ ምክንያቱም ምሥጢረ ሥጋዌ ሲባል በዚህ ዐውድ ተሠገወ፣ ሰው ሆነ፤ ተሰብአ ሰው ሆነ፤ የሚለውን የሚያስረዳ ቃል ነው፡፡

ምሥጢር በዓይን አይታይም፤ በእጅ አይዳሰስም፤ ረቂቁ አምላክ ግዙፉን ሥጋ ተዋሕዶ ሰው ሲሆን ተዳሰሰ፤ ተጨበጠ፤ ረቂቁ አምላክ ሰው የሆነበትን ጥበብ፣ የማይታየው የታየበትን፣ የማይዳሰሰው የተዳሰሰበትን ምሥጢር የምናስተምርበት ምሥጢረ ሥጋዌ ይባላል፡፡ ምሥጢረ ሥጋዌ የአምላክ ሰው የመሆን ምሥጢር ማለት መሆኑን ነው፡፡

## ሐመር፡- አምላክ ሰው የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?

**መልአከ ታቦር ኀይለ ኢየሱስ፡-** እግዚአብሔር አምላክ ይህን ዓለም የፈጠረው ስለ ሰው ፍቅር ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ “ዓለምን መፍጠሩ ሰውን መውደዱን ያስረዳል፡፡” (ተግሣጽ ዘዮሐንስ አፈ ወርቅ) በማለት እንደ ገለጠው በድርሳነ ቄርሎስም “እስመ በእንተ ሰብእ ገብረ ኵሎ፤ ሁሉንም ስለ ሰው ሲል ፈጠረው” ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን (ድርሳነ ቄርሎስ ፬፥፭) ሌሎች ፍጥረታት የተፈጠሩት ሰውን ለማገልገል ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ፀሐይ ለራሷ ጥቅም የላትም፣ ለሰው ግን ትጠቅማለች፡፡ ጨረቃም፣ ከዋክብትም ለሰው ይጠቅማሉ እንጂ ሰው ለፀሐይ፣ ለጨረቃ፣ ለከዋክብት የሚጠቅማቸው ነገር የለም፡፡ የላሞችን ወተት እኛ እንጠጣለን እንጂ ላሞች የእኛን አይጠጡም፡፡ የላሞችን፣ የበጎችን፣ የበሬዎችን ሥጋ እኛ እንበላለን እንጂ እነሱ የእኛን ሥጋ አይበሉም፡፡ ይህ ሁሉ የተደረገው ለሰው ልጅ ነው፡፡

ውኃ ለሰው ይጠቅማል እንጂ ሰው ውኃን አይጠቅመውም፡፡ዕፀዋት ሰውን ይጠቅሙታል እንጂ ሰው ዕፀዋትን አይጠቅምም፡፡ከ፳፪ ፍጥረታት ሰማይን ጨምሮ አምስቱ በሰማይ ሌሎቹ ደግሞ መሬትን ጨምሮ በምድር ያሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ የተፈጠሩት ለሰው ጥቅምና ክብር ነው፡፡ ለዚህ ክብር የተፈጠረው ሰው ይህ ሁሉ አልበቃው ብሎ ምክረ ከይሲን ሰምቶ፣ ዕፀ በለስን በልቶ፣ ሲፈጠር የነበረውን የጸጋ አምላክነት ትቶ የማይገባውን የባሕርይ አምላክነት ሽቶ አታድርግ የተባለውን አደረገ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፈ፡፡ በዚህ ጊዜ አምላክ በአምላክነቱ፣ ንጉሥ በመንግሥቱ፣ ጕልማሳ በሚስቱ የሚመጣባቸውን አይወዱምና አዳምና ሔዋን በአምላክነቱ ሲመጡበት ቀጣቸው፡፡

ዲያብሎስ በአምላክነቱ ሲገባ ወድቋል፣ አወዳደቁም የከፋ ነው፡፡ ለዘለዓለም እንዳይነሣ ሆኖ ወድቋል፡፡ ዲያብሎስን ማንም አላሳሳተውም የተሳሳተው ራሱ ነው፡፡ ሰው ግን የተሳሳተው በምክረ ከይሲ ነው፡፡አዳም በምክረ ከይሲ በተሳሳተ ጊዜ እግዚአብሔር አራት ከባድ ርግማኖችን አሳልፏል፡፡እነርሱም፡-

ሀ. **እባብን የረገመው፡-** እባብ ሲፈጠር እጅና እግር ነበረው፡፡ ሲረገም ግን እግር አልባ ሆኖ በልቡ እንዲሄድ ተደረገ፤ ምግቡም አፈር ሆነ፡፡መጽሐፍ ቅዱስ “እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው፤ ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት

ሁሉ፣ ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ሁን፤ በደረትህና በሆድህም ትሄዳለህ፤ በሕይወትህም ዘመን ሁሉ አፈርን ትበላለህ" በማለት እግዚአብሔር ያስተላለፈበትን ርግማን ያስረዳናል። ሌላ ምግብ ሳይበላ አፈር ብቻ በልቶ መኖር የሚችል ፍጡር እባብ ነው(ዘፍ.፫፥፲፬)።

ለ. **ሔዋንን የረገማት፡-** ምጥሽን፣ ጋርሽን፣ ጻዕርሽን አበዛዋለሁ። ከወለድሽ በኋላ ግን ፈቃድሽ ወደ ባልሽ ይሁን።አንቺ ዕፀ በለስን ቆርጠሽ እንዳደማሽት አንቺም በየወሩ እንዲሁ ደም ይፍሰስሽ ተብላ ተረግማለች።"ለሴቲቱም እግዚአብሔር እንዲህ አላት ጭንቀሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ከወለድሽም በኋላ ፈቃድሽ ወደ ባልሽ ይሆናል" እንዲል(ዘፍ.፫፥፲፮)።

ሐ. **አዳምን የረገመው፡-** አቀበት እንዲወጣ፣ ቁልቁለት እንዲወርድ፣ ላቡን አንጠፍጥፎ፣ ጥሮ ግሮ እንዲበላ "እግዚአብሔርም አዳምን አለው፤ የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና ከእርሱ እንዳትበላ ነው። ከአዘዝሁህ፣ ከዚያ ዛፍም በልተሃልና ምድር በሥራህ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፤ እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራህን ትበላለህ፤ አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና" በማለት ሊቀ ነቢያት ሙሴ እግዚአብሔር አምላክ በአዳም ላይ ያስተላለፈውን ርግማን ጽፎልን እናገኛለን (ዘፍ.፫፥፲፯-፲፰)።

መ. **ምድር፡-** እሾህና አሜከላ እንድታበቅል፣ ተረገመች። "ምድር በሥራህ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፤ እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች" እንዲል። እነዚህ እሾህ እና አሜካላ የተባሉት ፍትወታት፣ እኩያት፣ ኀጣውእ ሲሆኑ በአዳም ላይ ሠለጠኑ። በጸጋ እግዚአብሔር ይኖር የነበረው ሕጉን ከተላለፈና ከተረገመ በኋላ የነበረውን ሁሉ አጣ (ዘፍ.፫፥፲፯-፲፰)።

ከተረገሙ በኋላ አዳምና ሔዋን ተጸጸቱ፤ ስለበደላቸውም እጅግ አዘኑ፤ የፈጠራቸው አምላክ ንስሓቸውን ምክንያት አድርጎ ተስፋ እንይቆርጡ ተስፋ የሚፈነጥቅ ቃል ኪዳን ገባላቸው። ቃል ኪዳኑም "ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ እምርሃለሁ፤ ይቅርታም አደርግልሃለሁ፤ በይቅርታዬና በምሕረቴ ብዛትም ወደ አንተ ቤት እወርዳለሁ፤ በወገንህም ከርሥ አድራለሁ፤ይህ ሁሉ ስለ አንተ ድኅነት ይሆናል" የሚል ነበር (ቀለ.፫፥፲፬)።ወገንህ የተባለች ቅድስት ድንግል ማርያም ናት።

ለዚህ አስረጅ የሚሆነው "ይህን ሁሉ ስማ፤ ነገሬንም አድምጥ፤ ልብ ብለህም አድምጥ፤ የእግዚአብሔርም ቃል ከሰማይ ወደ ምድር ይወርዳል፤ ይህንንም እግዚአብሔር አምላኬ ከነገት ባስወጣኝ ጊዜ ነግሮኛል። ሕያው እግዚአብሔር ቃሉ በኋለኛ ዘመን ስሟ ማርያም ከምትባል ከአንዲት ድንግል ይወለዳል። አወላለዱንም ከእርሱ በቀር ማንም ሊያውቀው አይችልም በረቂቅ ምሥጢር ይወለዳልና" የሚለው ቃል ነው(ቀሌ. ፫፥፲፫)። ዓለምን ሊያድን የፈቀደው አምላክ ከማን እንደሚወለድ በግልጽ ይናገራል። ማርያም የሚለውን ስም ያወጣው እግዚአብሔር ነው። ድንግል ማርያም ደግሞ በነቢያት ትንቢት እንደ ተነገረው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም እንደ ነገራት ስትወልደው መድኃኔዓለም ብላ ስም አውጥታለታለች(ዝኒ ከማሁ)።

ቅዱስ ያሬድ "ወትቤሎ እሙ መድኃኔ ዓለም፣ ዮም ተወልደ ከሣቴ ብርሃን፣ እናቱ የዓለም መድኃኒት አለችው፤ ብርሃንን የገለጠው ዛሬ ተወለደ" በማለት እንደገለጠው ማለት ነው (ዚቅ ዘልደት)። ዓለም በተፈጠረ በሰባተኛው ዓመት እግዚአብሔር አብ ስሟ ማርያም ከምትባል ከድንግል ዘንድ ልጁን እንደሚልክውና በሥጋ ማርያም እንደሚወለድ ለአዳም የማይናወጥ ተስፋ ሰጥቶታል። "የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና" ተብሎ በቅዱስ ወንጌል የተጻፈውም የሚያስረዳን ይህን ነው(ሉቃ.፲፱፥፲)።

ስለዚህ አምላክ ሰው የሆነበት ዋናው ምክንያት በምክረ ከይሲ ተታሎ የወደቀውን ሰው ለማንሣት፣ የረከሰውን ለመቀደስ፣ የጠፋውን ለመፈለግ፣ የሞተውን ለማዳን ነው። ፈልጎም እንደ በግ እየጐተተ አልወሰደውም። ዮሐንስ አፈ ወርቅ "የጠፋ በግ አዳምን የፈለገው በአገኘውም ጊዜ የተሸከመው እውነተኛ ቸር ጠባቂ ከአንቺ የተወለደ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ" በማለት የገለጸውን ፈጽሞ ነው (ሃ.አበ.፷፰፥፴፮)። ተአምረ ማርያምን የጻፈልን ደቅስዮስም ይህን የዮሐንስ አፈ ወርቅን ቃል ጠቅሶ እንደገለጸው የጠፋውን ለመፈለግ ሰው ሆነ።ስለዚህ ለምን ሰው ሆነ ከተባለ የሞተውን ሊያድን ነው።

ሁለተኛው አምላክ ሰው እንዲሆን ያደረገው የሰው ፍቅር ነው።አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም "ፍቅር ኃይል ወልድን ከመንበሩ ሳበው እስከ ሞትም አደረሰው" በማለት እንደ ገለጠው የሰው ፍቅር ስቦት ሰው ሆነ።ዙፋኑ ያለው ጽርሐ አርአያም ነው። ከጽርሐ አርያም ከዙፋኑ የሳበውና ሰው እንዲሆን ያደረገው የሰው ፍቅር ነው።

በመጀመሪያ በመልኩ ፈጠረው፤ ከዚያም የሚወደውና በአርአያው የፈጠረው ሰው ቢወድቅበት ወድቆ እንዲቀር ስላልፈቀደ የእሱን መልክ የእሱን ሥጋ ተዋሕዶ ሰው ሆኖ አዳነው። ጌታችን "መቶ በጐች የነበሩት ሰው ቢኖር ከእነርሱ አንዲቱ ብትጠፋበት ዘጠና ዘጠኙን በምድረ በዳ ትቶ እስኪያገኛት ድረስ ይፈልጋት ዘንድ ወደ ጠፋችው ይሄድ የለምን? በአገኛትም ጊዜ ደስ ብሎት በትከሻው ላይ ይሸከማታል።" ብሎ መቶ በጎች ባሉት ባዕለ ጸጋ መስሎ ያስተማረው እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር የሚገልጥ ነው (ሉቃ.፲፭፥፬-፭)።መላእክት በጥንተ ተፈጥሮ በነገድ መቶ ነበሩ። ከመቶ ነገድ አንዱ ዲያብሎስ ወጣ፣ መቶኛ ሆኖ የተተካው አዳም ነው። ስለዚህ ከመቶ ነገደ መላእክት አንዱ የነበረው አዳም መሳሳት የአጋንንት መጫወቻ እንዲሆን አድርጎታል። ለ፶፻፭፻ ዘመን ‹‹አሁንም የዚህ ዓለም ፍርድ ደረሰ፤ ከእንግዲህ ወዲህ የዚህን ዓለም ገዥ ወደ ውጭ አስወጥተው ይሰዱታል" (ዮሐ.፲፪፥፴፩) ብሎ ጌታችን መድኃኒታችን እንደ

ተናገረው ጊዜው ደርሶ ከሥልጣኑ ማለትም ይህን ዓለም የሚገዛበት ሥልጣን እስኪሻር ድረስ ዲያብሎስ በሰው ልጅ ላይ ነግሦ ነበር፡፡

ስለዚህ የሰውን ልጅ ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ ለማውጣት፣ ሰውን ለመቀደስ፣ የጠፋውን ለመፈለግና የሞተውን ለማዳን ሰው ሆነ፡፡

***ሐመር፡- "ሰው ሆነ" የሚለው ቃል "በእኛ አደረ" ከሚለው ቃል ጋር እንዴት ይታረቃል? ይህ አባባልስ ውላጤን (መለወጥን) እና ኅድረትን አያመለክትም ወይ?***

***መልአከ ታቦር ኀይለ ኢየሱስ፡-*** *ለምሥጢረ ተዋሕዶ የሚነገረው ቃል ይህ ነው፡፡ ለሁሉቱም የተሰጠ መልስ አለ፡፡ ተሰብአ ያለውን ገጸ ንባብ ይዘው ሰብአ ውላጤ የሚባሉት ወይም በውላጤ የሚያምኑት ከሓዲዎች በኑፋቄ ስማቸው ሐራ ጥቃ ይባላሉ፡፡ እነርሱ ተለወጠ እንዳይሉ ኀደረ አለባቸው፡፡ኀደረ ያለውን ይዘው ደግሞ ሰብአ ኅድረት እንደነ ንስጥሮስ ያሉት በኅድረት ከበረ እንዳይሉ ተሰብአ አለባቸው፡፡ ተሰብአ እና ኀደረ እንደ አለቃና ጠበቃ ይጠባበቃሉ በማለት ትርጓሜ ውዳሴ ማርያም ይነግረናል፡፡ ይህ ማለት ተሰብአ ኅድረትን ይጠብቃል፤ ኀደረ ውላጤን ይጠብቃል፡፡ ይህ ማለት ተሰብአን ይዘው ውላጤ ለሚሉት ኀደረ መልስ ይሆናቸዋል፡፡ ኀደረ የሚለውን ይዘው ኅድረት ለሚሉት ደግሞ ተሰብአ የሚለው መልስ ይሆናል፡፡*

*ኀደረ ማለት ምን ማለት ነው? ስንል የእኛን ሥጋ ተዋሕዶ በእኛ ላይ አደረ ማለት ነው፡፡ ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ዘተሰብአ ወኀደረ ለዕሌነ›› እንዲል የሰኞ ውዳሴ ማርያም፡፡ በእኛ አደረ የተባለው የእመቤታችን ባሕርይና የእኛ ባሕርይ አንድ ስለሆነ ነው፡፡ የእመቤታችን ግብርና የእኛ ግብር አንድ አይደለም፡፡ ክርስቶስም የተዋሐደው የእኛን ባሕርይ እንጂ ግብራችንን አይደለም፡፡ ግብራችን ኃጢአትም፣ ጽድቅም ለመሥራት ዝግጁ ነው፡፡ ኃጢአት የባሕርይ አይደለም፡፡ ስለዚህ ባሕርያችንን ተዋሕዶ በእኛ ላይ አደረ ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ ተሰብአ ቢልም ሰው ሆነ ማለት ነው፡፡ ኀደረ ቢልም የእኛን ሥጋ ተዋሕዶ ሰው ሆነ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ከምሥጢረ ተዋሕዶ የወጣ ትርጕምም፣ አስተምህሮም የለም፡፡*

በነቢያት አደረ የሚለው ቃል በረድኤት ማደሩን የሚገልጥ ነው፡፡ በእመቤታችን ግን ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሆነ ማለት ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በእጅ ተዳስሷል፡፡ ሰው ካልሆነ እንዴት ተዳሰሰ፣ በላ ጠጣ፣ ተራበ ይባላል? ዘአልቦ ጥንት ኮነ ቅድመ ወለዘ አልቦ መዋዕል ኮነ ሎቱ መዋዕል፡፡ ከፅንሰቱ እስከ ልደቱ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ተብሎ ተቈጠረለት፡፡ ቤተ ግዝረት እስኪገባ ፰ ቀን ተብሎ ከዚያም ፲፪ ዓመት ተብሎ፣ ሲጠመቅ ፴ ዓመት ተብሎ ተቈጠረለት፡፡ ይህ ዘመን የተቈጠረለት ሥጋን የተዋሐደ መለኮት ዘመን ተቈጠረለት፣ቅድምና ያልነበረው አምላክ ቀዳማዊ ተባለ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናና ዛሬ እስከ ዘለዓለምም የሚኖር እርሱ ነውና" (ዕብ.፲፫፥፰) በማለት የተናገረለትን አምላክ "ጾርኪዮ በከርሥኪ ተስዓተ አውራኀ፣ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅፀንሽ ተሸከምሽው" ተብሎ በአንዲት ብላቴና ለዚህን ያህል ጊዜ ተወሰነ ተባለ፡፡

***ሐመር፡- ምሥጢረ ሥጋዌን ለክርስቲያኖች በቀላል ምሳሌ ማስተማር የምንችለው እንዴት ነው?***

***መልአከ ታቦር ኀይለ ኢየሱስ፡-*** *ረቂቅ ምሥጢር በያዘው ሃይማኖተ አበው ቅዱስ ቄርሎስ "በእግዚአብሔር ቃል በረቂቅ ባሕርይ የሆነውን ተዋሕዶ አንካድ፤ ብረት ከእሳት ጋር በተዋሐደ ጊዜ ከእሳትም በመዋሐዱ የእሳትን ባሕርይ ገንዘብ እንዲያደርግ ብረት በመዶሻ በተመታ ጊዜ ከእሳት ጋር በመዶሻ እንደሚመታ ግን ከመዶሻው የተነሣ የእሳት ባሕርይ በምንም በምን እንዳይጎዳ ሰው የሆነ አምላክ ቃል በመለኮቱ ሕማም ሳይኖርበት በሥጋ እንደታመመ  እናስተውል" በማለት በግልጽ ተናግሯል(ሃ.አበ.፸፯፥፲፪)፡፡*

የሊቁን ምሳሌ በትክክል የሚረዳው የአንጥረኛን ተግባር የሚያውቅ ሰው ነው፡፡ አንጥረኛው ብረቱን ከእሳት ውስጥ ሲያስገባው ብረቱ ይግላል፡፡ ባለሙያው የጋለውን ብረት ማረሻ፣ ማጭድ፣ ቢላዋ አድርጎ ያበጀዋል፡፡ አንጥረኛው የሚመታው ብረቱን ነው፡፡ብረቱ ሲመታ እሳቱ የቅርፅ ለውጥ አይታይበትም፡፡እሳቱ እንደ ብረቱ አይቀጠቀጥም፡፡

ሮማውያን ካቶሊክ ከመሆናቸው አስቀድሞ የሮም ሊቀ ጳጳስ የነበረው ሰለባስትርዮስ ኖጎ ይባል ከነበረ አይሁዳዊ ጋር ባደረገው ክርክር "ዛፍ ቢኖር ብርሃነ ፀሐይ በቀትር ጊዜ ወድቆበት ሳለ በምሳር እንቆርጣለን ቢሉ ዛፉን በምሳር በመቱት ጊዜ ፀሐይ ወድቆበት ሳለ የብረቱ ኃይል በግንዱ ላይ የሚወድቅ አይደለምን? አይሁዳዊ ኖጎም እውነት ነው አለ፡፡ ሰለባስትርዮስም ፀሐይ በምሳሩና በዛፉ ላይ ወድቆባቸው ሳለ ምሳር ፀሐይን ይቆርጠው ዘንድ ወይም ክርክራት፣ ፍልቃት ያደርግበት ዘንድ ይቻለዋልን? አለ ኖጎም አይቻለውም አለ፡፡ ሰለባስትርዮስም ስለ ክርስቶስ ሕማም ሞት የምንናገረው እንደዚህ ነው፡፡ ሥጋው በዛፍ፣ ሕማሙ በምሳር፣ መለኮትም በፀሐይ ይመሰላል፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮቱን ከሕማም ወገን ምንም ያላገኘው እንዲሁ በሥጋ ታመመ አለው" (ሃ.አበ. ፵፫፥፪-፬)፡፡ ምሥጢረ ሥጋዌን ስናነሣ ደግሞ ልደቱን ብቻ ሳይሆን ሰው ሆኖ የሠራውን ድንቅ ሥራ ሁሉ እንጠቅሳለን፡፡

ቃል ይሰማል እንጂ አይታይም፤ ጽሑፍ ላይ ሲቀመጥ ግን ይታያል፡፡ በሚታይና በሚዳሰስ ሲፈጸም ይረዳልና፡፡ ይህን በተመለከተ ቴዎዶጦስ "ከአንደበታችን የሚወጣ እርስ በእርሳችን የምንነጋገርበት የእኛ ቃል አለ፤ ማንም ማን ሊያየው አይችልም፤ ለቃል ግዘፍ የለውምና፤ ለማንም ለማን አይታይምና፤ በእጅም አይዳሰስምና፤ ቃል በብራና በተጻፈ ጊዜ፣ ቅርፅም በሆነለት ጊዜ፤ ያን ጊዜ የተገለጠ ይሆናል፤ ይታያል፤ ይዳሰሳል እንጂ" በማለት ያስረዳል (ሃ.አበ.፶፫፥፲፫)፡፡

አስቀድመን የጠቀስናቸው ሊቃውንት ያስተማሩት ዕለት ዕለት በሕይወታችን በምንጠቀምበት ነገር እየመሰሉ ነው፡፡በቀላል መንገድ ማስተማር ማለት ደግሞ እንዲህ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ምሥጢረ ሥጋዌ መባሉንም መዘንጋት የለብንም፡፡ ነገረ እግዚአብሔር፣ ነገረ ሥጋዌ፣ ነገረ ክርስቶስ በእምነት፣ በንጽሐ ነፍስ፣ በንጽሐ ሕሊና ሲወሰኑ የሚገለጥ ጭምር እንጂ በትምህርት ብቻ የሚገለጥ ጉዳይ አለመሆኑን መዘንጋት አይገባም፡፡✤